# <<እጅግ የበዛው ጩኸት - መብት ወይንስ ርኩሰት?>>

**ማሳሰቢያ፤**

**ከ14 ዓመት በታች የሆኑ ልጆች ይሄንን ዘጋቢ ፊልም እንዲያዩት አናበረታታም!**

ከሁሉ አስቀድመን ስለግብረሰዶማዊነት ስንነጋገር፣ ይህ ርእስ በአገራችን በአሁኑ ጊዜ በሃይማኖታችንም ሆነ በባሕላችን ፍጹም ጸያፍ ነገር እንደመሆኑ አንዳንድ አድማጮች ምናልባት ነውርና ዘግናኝ ነገሮች ሲጠቀሱ ጥቂት የሚቀፍና እረፍት የማይሰጥ ሊሆንባችሁ እንደሚችል እናስባለን። ይሄንን ርእስ እንደሚገባው ለመመልከትና በተለያዩ አቅጣጫዎችም ለመቃኘት አንዳንድ ለስሜት የሚቀፉ ነገሮችን ማንሳት ግድ ስለሚሆን አድማጮች ይህንን እንድትታገሱልን በትህትና እንጠይቃለን።

> "ፍሬም ከሌለው ከጨለማ ሥራ ጋር አትተባበሩ፥ ይልቁን ግለጡት እንጂ፥ እነርሱ በስውር ስለሚያደርጉት መናገር እንኳ ነውር ነውና፤ ሁሉ ግን በብርሃን ሲገለጥ ይታያል፤ የሚታየው ሁሉ ብርሃን ነውና።" (ኤፌሶን 5፥11-13)

**አብይ ርእስ (Theme)፤**
Pulling down the citadels of Satan!
**የሰይጣንን መንግስት ምሰሶዎች መደርመስ፤**

<<የሰዶምና የገሞራ ጩኸት እጅግ በዝቶአልና፥ ኃጢአታቸውም እጅግ ከብዷልችና>> (ትእይንት 1 መጀመሪያ)

## መግቢያ፡- ይሄንን ዘጋቢ ፊልም እንድናዘጋጅ የተነሳሳንበት ምክንያት

<<የሰለጠኑ ናቸው>> ወይንም <<ያደጉ አገሮች ናቸው>> ተብለው በሚታሰቡ የምእራባውያን አገሮች የምንኖር ኢትዮጵያውያን በእነዚህ አገሮች ውስጥ የሚካሄደውን የተለያየ የሕብረተሰብ ክስተት ከውጭ እንዳለ ሰው ሆነን (በሌላ መነጽር) ለማየት ልዩ እድል አለን። ስለግብረሰዶማዊነት በምእራቡ አለም ያለው ግንዛቤና መረዳት ለእኛ ለኢትዮጵያውያን ፍጹም ባይተዋርና ለመቀበል ፍጹም የሚያዳግት እንግዳ ነገር ነው። የግብረሰዶማዊነት አራማጅ ድርጅቶችም በእነዚህ የምእራባውያን አገሮች ምን ያህል ስፍራ እንዳገኙና ሕብረተሰቡን ወዳልሆነ አቅጣጫ እንዲያፈነግጥ ምን ያህል እየመሩ እንደሆነ በታላቅ ትዝብት እንመለከታለን። ይህ የኑሮ ዘይቤ ምን ያህል አፍራሽ፣ ክፉና አደገኛም ተጽእኖ እንደሆነ ለአገራችን ለኢትዮጵያ ማስገንዘብና በውጭው አለም ምን ያህል ጉዳት በግለሰብ፣ በቤተሰብና በማሕበረሰቡ ላይ እየመጣ መሆኑን ማስገንዘብ ኢትዮጵያዊ ግዴታችንና አደራችን እንደሆነም እናምናለን። ከምንም በላይ አገራችን ምእራባውያን አገሮች ወደዘቀጡበት የሞራል ዝቅጠት እንዳትወርድና ይልቁንም ባሕሏን፣ ሃይማኖቷንና አኩሪ ታሪኳን እንድትጠበቅና በዚህ ረገድ ከሚመጣባት እጅ አዙር የባሕል ቅኝ ግዛት እንድትጠበቅ ለማድረግ የበኩላችንን አስተዋጽኦ ለማድረግ እንወዳለን። ከዚህ በተረፈም በማወቅም ይሁን ባለማወቅ የተሳሳተና ሚዛንን ያልጠበቀ መረጃ በማቅረብ ግብረሰዶማዊነትን በተመለከተ ኢሳይንሳዊ የሆነ መረዳትን በመፍጠር የግብረሰዶማዊነት አራማጆች በስውር አጀንዳና በቅስቀሳ (በሎቢ)፣ ሕብረተሰባችንን

ወዳልሆነ አቅጣጫ እንዳይመሩት ሚዛናዊ መረጃዎችን ለአድማጮች ለማቅረብ በዚህ ዘጋቢ ፊልም ጥረት እናደርጋለን።

በዚህ ዘጋቢ ፊልም መልስ ልንሰጥባቸው ከምንሞክራቸው ጥያቄዎች መካከል፤

1) የግብረሰዶማዊነት መንስኤ ተብለው የሚታሰቡ ነገሮች ምን ምንድን ናቸው? (መሰረት ዓለሙ)
2) ሳይንስስ በዚህ ጉዳይ ምን ይላል? መሆኑን በተፈጥሮ (በጂን ውስጥ) ያለ ነገር ነውን? (ግሩም አለባቸው)
3) ይሄንን የኑሮ ዘይቤ የምንቃወመው ለምንድነው? መዘዞቹ ምንድን ናቸው? (አልዓዛር ገዳሙ)
4) ምእራቡ አለም የደረሰበት አሳዛኝ ደረጃ ምን ይመስላል? (ዮሐንስ ዓ.)
5) የግብረሰዶማዊነት አራማጆች (የሆሞ ሎቢ) አጀንዳና ስውር አሰራር ምን ምንድን ናቸው? (ዮሐንስ ዓ.)
6) በአገራችንና በሌሎችም ድሃ አገሮች ላይ ምእራቡ አለም ግብረሰዶማዊነትን ለማስፋፋት እያካሄደ ያለው ቅስቀሳ አለን? (መሰረት ዓለሙ)
7) ቅዱሳት መጻሕፍት ስለግብረሰዶም ጉዳይ ምን ይላሉ? (ሳምሶን ሲሳይ)
8) ከግብረሰዶማዊነት ወጥቶ ጤናማ ወደሆነ የወንድና የሴት ግንኙነት ውስጥ መግባት ይቻላልን? (ኤርምያስ ቃለአብ)
9) ልጆች ግብረሰዶም እንዳይሆኑ መከላከል የሚቻለው እንዴት ነው? (መሰረት ዓለሙ)
10) በግብረሰዶማዊነት የሚኖሩ ግለሰቦችን ልናያቸው የሚገባው እንዴት ነው? (አልዓዛር ገዳሙ)
11) ይሄንን ተጽእኖ ለመከላከል በግለሰብ ደረጃ፣ በቤተሰብ ደረጃ፣ በቤተ-እምነቶች ደረጃና በሕብረተሰብ ደረጃ ማድረግ የምንችለው ምን ምንድነው? (ዮሐንስ ዓ.)

የሚሉት ይገኙባቸዋል።

የዘጋቢ ፊልሙ ዓላማ (ግብ)፤

- የግብረሰዶማዊነት ክስተት ከተፈጥሮ ውጪ የሆነ ክፉ የኑሮ ዘይቤ መሆኑን በማስገንዘብን የሞራል ጥያቄ እንጂ የመብት ጥያቄ እንዳይደለ በትክክል ለማስገንዘብ።
- የሰዶማዊነት ሕይወት ግብረሰዶም የሆነውን ግለሰብ እራሱን፣ ልጆችን፣ ማሕበራዊ ኑሮንና ሕብረተሰብን ምን ያህል እንደሚጎዳና እንደሚያፈርስ በሳይንሳዊ ጥናት የተጠናቀሩ መረጃዎችን ለማቅረብና ለማሳየት።
- በአገራችንና በሌሎችም ድሃ አገሮች ላይ ምእራቡ አለም የገንዘብና የእርዳታ ጥገኝነታችንን መሳሪያ በማድረግ ይሄንን ክፉና ጸያፍ የኑሮ ዘይቤ በሰብአው መብት ሽፋን አሹልከው ወደአገራችን እንዳያስገቡ የተለያዩትን የሕብረተሰብ ክፍሎችን ማሳሰብና ማንቃት።
- ግብረሰዶማዊነትን በአገራችን ለማራመድ ከምእራቡ አለም እየተደረጉ ያሉትን እርምጃዎች በተጨባጭ ማስረጃዎች ለማጋለጥ።
- እናት አገራችንን ይሄንን ክፉ ርኩሰት ስታስተናግድና ስታቅፍ እንዳትገኝ የበኩላችንን ማስጠንቀቅ ለማቅረብ።

- በስዊድንና በምእራባውያን አገሮች የግብረሰዶማዊነት አራማጆች በስውር የሚሰሩትን ስራና የሚነዙትንም እውነት መሳይ ሃሰቶችን በገሃድ አውጥቶ ማጋለጥ።
- <<እግዚአብሔር ሃጢአትን ይጠላል ሃጢአተኛውን ግን ይወዳል>> በሚለው ጽኑ መርሆ መሰረት ሰዎች ወደ ግብረሰዶማዊነት ኑሮ በብዙ ምክንያት ሊገቡ እንደሚችሉ በማመልከት በዚህ ኑሮ የሚገኙ ሰዎች ሊታዘንላቸውና በእግዚአብሔር ርሕራሄ ሊታዩ እንደሚገባቸው ለማመልከት
- የሃይማኖት ተቋማትና ድርጅቶች በዚህ ኑሮ የተጠመዱትን ሊረዱና ከዚህ ኑሮም ሰዎችን ለማላቀቅ የሚችሉበትን እውቀትና ቅድመ ዝግጅት እንዲያደርጉ አበክሮ ለማሳሰብ።

በዚህ ክፉ ኑሮ የተጠመዱ ግለሰቦች ከዚህ መላቀቅ እንደሚችሉ ለማሳሰብና ተስፋ እንዳላቸው ለማወጅ።

**<u>በዘጋቢ ፊልሙ የምንጠቀምባቸው በጣም ያልተለመዱ ቃላት ዝርዝርና ትርጉማቸው፤</u>**

**ሄትሮሴክሹአሎች፤** ከተቃራኒ ጾታ ጋር ብቻ ግንኙነት የሚያደርጉ ግለሰቦች፤ Hetro sexuals (አብዛኛዎቻችን የሆነውን ያመለክታል) (አልዓዛር ገዳሙ)

**ግብረሰዶማውያን / ከተመሳሳይ ጾታ ጋር ዝሙት የሚያደርጉ ግለሰቦች (ወንድም ሆነ ሴት ሊሆን ይችላል)፤** ወንድ ከሆኑ gays ይባላሉ። ሴቶች ግን gay ም lesbianም ተብለው ይጠራሉ።

**ባይሴክሹአል ግለሰቦች - ከተቃራኒ ጾታ ጋርም ከተመሳሳይ ጾታ ጋርም ግብረስጋዊ ግንኙነት የሚያደርጉ ግለሰቦች፤** Bisexuals individuals (መሰረት ዓለሙ)

**ትራንስሴክሹአል ግለሰቦች፤** ጾታቸውን የቀየሩ ግለሰቦችን ያመለክታል፤ trans-sexuals

**አፍቃሬ-ሕጻን - ለአቅመ አዳም ካልደረሰ ልጅ ወይንም ከሕጻን ጋር ግብረስጋዊ ግንኙነት የሚያደርግ፤** በእንግሊዝኛ Paedophile፣ (አልዓዛር ገዳሙ)

**ሕጻን ደፋሪ፤** child molester, sexual predator (አልዓዛር ገዳሙ)

**የግብረሰዶማዊነት አራማጆች፤** ግብረሰዶማዊነትና ግብረሰዶማውያን በሕብረተሰብ ተቀባይነት እንዲኖራቸው በተለያየ መንገድ በትጋት የሚሰራ፣ gay activist

# የግብረሰዶማዊነት መንስኤዎች

ስለግብረሰዶማዊነት መነሾዎች ብዙ ሰዎችና ድርጅቶች የተለያዩ ምክንያቶች ናቸው የሚሉአቸውን ሃሳቦች ሰንዝረዋል። በተለይም በአራማጆቹ ከሚጠቀሱት ምክንያቶች አንዱ ግብረሰዶማዊነት በዘረመል (በጂን) ውስጥ ያለ ነገር ነው የሚለው ሲሆን ለዚህ መላምት ግን ሙሉ በሙሉ ድጋፍ የሚሆን ሳይንሳዊ ማረጋገጫ አልተገኘለትም።

ዶክተር Joseph Nicolosi በአሜሪካ ከ20 ዓመት በላይ ግብረሰዶም የሆኑና ከግብረሰዶማዊነታቸው መላቀቅ የሚፈልጉ ግለሰቦችን ሲረዱ የኖሩ የስነ ልቦና ጥናት ተመራማሪ ሊቅና NARTH (National Association for Research & Therapy of Homosexuality) የተባለው ግብረሰዶማውያንን ለመርዳት የቆመ ድርጅት ፕሬዚዳንት ናቸው። እኚሁ ሊቅ እ.ኤ.አ. በ2002 ባሳተሙት *A Parent's Guide to Preventing Homosexuality* በሚል መጽሐፋቸው ለግብረሰዶማዊነት መነሾ ናቸው ብለው ካቀረቡአቸው ምክንያቶች መካከል የሚከተሉትን ጠቅሰዋል፤

1. ለግብረሰዶማዊነት ዋነኛው መንስኤ ተደርጎ የሚታሰበው በልጅነትና በጉርምስና እድሜ የሚፈጠር የጾታ ግንዛቤ መዛባት (Gender Identity Disturbance) ይላሉ!

እኚሁ ሊቅ እንደሚሉትም ወንዶች ልጆች ለጾታ ግንዛቤ መዛባት የሚጋለጡት ከእናታቸው ጋር ያላቸውን መያያዝ ቀነስ አድርገው ከአባታቸው ጋር በቂ ጊዜ በማሳለፍ ተባእታዊ የጾታ ግንዛቤን (ማስክዩሊኒቲን) ለማሳደግ ሳይችሉ ሲቀሩ ነው። በተጨማሪም ልጆች ከአባታቸው ጋር ፍጹም የተበላሸና ፍቅር የለሽ ግንኙነት ሲኖራቸው ለፆታ ግንዛቤ መዛባት ይጋለጣሉ። (ሳምሶን ሲሳይ)

2. ወንዶች ልጆች በሴት መጫወቻ ሲጫወቱ፣ የሴት ልብስ ሲለብሱ፣ ከሴት ልጆች ጋር ብቻ ሲጫወቱ ወ.ዘ.ተ. ቀስቃሽ ደወል ሊሆን ይገባል!
3. በምእራባውያን ትምሕርት ቤቶች ውስጥ በግብረሰዶማዊነት አራማጆች ግፊት ጥላቻን (ባያስን) ለማጥፋት ተብሎ <<ግብረሰዶማዊነት ምንም የለበትም>>፣ <<ያለ ነገር>> (ኖርማል) ነው፣ <<የምርጫ ጉዳይና ከሄትሮስክሹአልነት ምንም የማይለይ ነው>> ተብሎ ስለሚቀርብ ይህ የተዛባ ሚዛን የለሽ አቀራረብ የጾታ ግንዛቤ መዛባት አደጋ እድሜ ላይ ያሉትን ልጆችንና ታዳጊ ወጣቶችን ብዙ ችግር ላይ ሊጥል እንደሚችል ማየት አዳጋች አይደለም።

ከዚህ በተረፈ፤

4. የሞራል ልቅነት በበዛበት ሁኔታ አንዳንዶች በግብረስጋ ግንኙነትን ዙሪያ በሚደረግ ልዩ ልዩ ሙከራ ምክንያት ወደዚህ ሕይወት ሊገቡ እንደሚችሉ ይታወቃል፡፡ ምእራባውያን አገሮች ግብረሰዶማዊነትን ሊሞከርና ሊፈተሽ እንደሚገባው ልምምድ አድርጎ እስከመሳል ድረስ ደርሰዋል፡፡ ይሄ ደግሞ የጾታ ግንዛቤ መዛባት አደጋ ላይ ያሉ ሰዎችን ወደዚህ ልምምድ ሊዘፍቃቸው እንደሚችል ግልጽ ነው!

በሃገራችን የተደረገ አንድ ጥናት እንደሚያሳየው፤

5. የጎዳና ተዳዳሪ በሆኑ ታዳጊ ወጣቶች መካከል በተመሳሳይ ጾታ የተደፈሩ ብዙዎች ለዚህ ኑሮ ሰለባ ሆነው ሳይወዱት ለግብረሰዶማዊነት ለኤድስና ለሌሎች በሽታዎች የተጋለጡ እንደሚሆኑ ይገልጻል።
6. ግብረሰዶማዊነት በምድራችን በጣም ከተስፋፋባቸው ስፍራዎች አይነተኛው እስር ቤቶች ናቸው። ብዙዎቹ በእስር ቤት ሳሉ ይሄንን ሕይወት የተለማመዱ ግለሰቦች ከተፈቱ በኋላ ሄትሮሴክሹአል ወደሆነው ሕይወት ቢመለሱም እንኳን ገሚሶቹ ግን በዚያው ሕይወት ሊቀጥሉ እንደሚችሉ ማሰብ አዳጋች አይሆንም።

ሌሎች ለግብረሰዶማዊነት መነሾ ሊሆኑ ይችላሉ ተብለው በሙያተኞች ከሚታመንባቸው ምክንያቶች መካከል፤

7. ደካማ አባትና ሃይለኛ እናት በልጆች አስተዳደግ ላይ የሚያስከትሉት የሚዛን መዛባት
8. ተለቅ ባለ ሰው ወሲባዊ ማባበል መታለል (ሴዳክሽን) የደረሰባቸው ታዳጊዎች እንዲሁም በሕጻንነታቸው የተደፈሩ ልጆች እንደዚያ የመሆን እድላቸው ከፍ ያለ ነው!

ሆኖም ከእነዚህ ከተጠቀሱ ምክንያቶች ውጭ ለምሳሌ ከድህነት የተነሳ ለዚህ ሕይወት የሚዳረጉ ሰዎች እንደሚኖሩ መዘንጋት የለብንም። ከኑሮ ችግር የተነሳ ሰውነታቸውን ለተመሳሳይ ጾታ ግንኙነት በማቅረብ ወጥመድ ወደሆነ ወደዚህ ልምምድ ሰዎች ሊገቡ ይችላሉ።

# ሳይንስ በግብረሰዶማዊነት ዙርያ ምን ይላል?

ሌላው በግብረሰዶማዊነት ዙርያ በአሁኑ ጊዜ በምእራቡ አለም እየተሰማ ያለው ሃሳብ ደግሞ የወሲብ ዝንባሌ በዘር የሚወረስ፣ በዘረ-መል (ጂን) ውስጥ የተቀመጠ ስለሆነ ይሄንን ይዘው የተወለዱ ህጻናትን ሲያድጉ ግብረሰዶማዊያን ከመሆን ሊያግዳቸው የሚችል ምንም መንገድ አይኖርም የሚል ነው፡፡ የተለያዩ የጥናት ውጤቶችም ይሄንን እንደሚያመለክቱ በመገነኛ ብዙሃን ሲዘገብ ተሰምቷል፡፡ በዚህ አቅጣጫ ከቀረቡት የጥናት ውጤቶች አንዳንዶቹን እስቲ እንመልከት፡፡

- የዘረ-መልን መላምት ለመፈተሽ ትኩረት የሳበው በመንትዮች ላይ ጥናት ማካሄድ ነበር፡፡ ከነዚህም ጥናቶች አንዱ እ.ኤ.አ. በ 1991 ቤይሊና ፒላርድ (Bailey – Pillard) ይዘውት የቀረቡት ነው፡፡ የሄው የጥናት ውጤትም ከፍተኛ ትኩረትን የሳበና በስፋት በመገናኛ ብዙሃን የተዘገበለት ነበር፡፡ ጥናቱን ካካሄዱት ውስጥ አንደኛው የሆነው ፒላርድ ግብረሰዶማዊ ሲሆን ቤይሊ ግን አልነበርም፡፡ በጥናቱ የተዘገበው ውጤትም የሚከተለው ነው፡፡

  ከአንድ እንቁላል የተገኙ መንትዮች (monozygotic twins) 52%
  ከሁለት እንቁላል የተገኙ መንትዮች 22%
  መንትያ ያልሆኑ ወንድማማቾች 9%
  የጉዲፈቻ ወንድማማቾች 11%
  ተመሳሳይ ወሲባዊ ዝንባሌ አላቸው የሚል ነው፡፡

| Bailey & Pillar Study () | | |
|---|---|---|
| Study using gay men from Gay magzines. | | |
| ከአንድ እንቁላል የተገኙ መንትዮች | | 52% |
| ከሁለት እንቁላል የተገኙ መንትዮች | | 22% |
| መንትያ ያልሆኑ ወንድማማቾች | | 9% |
| የጉዲፈቻ ወንድማማቾች | | 11% |

ውጤቱ የሚያመለክተውም ከአንድ እንቁላል የተገኙ መንትዮች አንደኛው ግብረሰዶማዊ ከሆነ ሌላኛውም እንዲሁ የመሆኑ እድል (concordance) 52% ነው የሚል ነው፡፡ ቤይሊና ፒላርድ ዘገባቸውን ሲያቀርቡ የብዙዎች መደምደሚያ፣ ምንም እንኳ ይሄንን የሚያረጋግጥ 100% መመሳሰል ባይገኝም፣ ግብረሰዶማዊነት በአመዛኙ በዘረ-መል (ጂን) ውስጥ ያለ ነው የሚል ነበር፡፡ ነገር ግን ማናቸውም ሳይንሳዊ የጥናት ውጤት ተአማኒነቱ የሚጸናው በሌሎች ተመሳሳይ ጥናቶች ውጤቱ ሳይፋለስ በድጋሚ ሲረጋገጥ ከቻለ ብቻ ነው፡፡ ነገር ግን ከዚህ ጥናት ቀጥሎ የተደረጉ ሌሎች ጥናቶች ተመሳሳይ ውጤት ሊያገኙ አልቻሉም፡፡ በጊዜው ለብዙዎች ያልታወቀው ነገር ለጥናቱ ናሙና ሆነው የተወሰዱት ሰዎች የተመረጡበት መንገድ እና ናሙናው ወደ አንድ ወገን ያጋደለ (biased) መሆኑ ነው፡፡ በኋላ እንደተጋለጠው ግን፣ ፒላርድ ራሱ ግብረሰዶማዊ እንደመሆኑ፣ ጥናቱ የሚካሄድባቸውን ሰዎችም ለማግኘት የተጠቀመበት መንገድ በግብረሰዶማዊ ጋዜጦች ላይ ማስታወቂያዎችን በማውጣት ነበረ፡፡ ከዚህም የተነሳ

ጥናቱ ሁሉን አቀፍና ሚዛናዊ ሳይሆን ከመነሻው ወደተፈለገው መደምደሚያ ሊያደርስ የሚችል ናሙና በመምረጥ የተካሄደ ነበር ማለት ነው፡፡

- ይሄ ሁኔታ ከተጋለጠ በኋላ ስሙ የጎደፈው ቤይሊ፣ ፒላርድን በመተው ከማይክል ዳን (Michael Dunne) እና ኒክላስ ማርቲን (Nicholas Martin) ጋር በዚሁ አቅጣጫ ጥናቱን ቀጠለ፡፡ በዚህ ጊዜ ግን እንደቀደመው የቤይሊና ፒላርድ ምርመራ ቁንጽል ተሳታፊዎች በመያዝ ሳይሆን በድፍን አውስትራልያ ከተመዘገቡ የአንድ እንቁላል መንትዮች የተወሰደ ናሙና ለጥናቱ እንዲጠቀሙ እድል አገኙ፡፡ ውጤታቸውም ከቀደመው የተለየ ሆነ፡፡ በዚህ ጥናት መሰረት በአንድ እንቁላል መንትዮች መካከል 11% ተመሳሳይነት ያለው የወሲብ ዝንባሌ ሲታይ
በሁለት እንቁላል መንትዮች ማካከል ግን ምንም አይነት መመሳሰል አልተገኘም፡፡

| Bailey, Michael Dunne & Nicholas Martin | | |
|---|---|---|
| Subjects: Statistics from all twins in Australia! | | |
| ከአንድ እንቁላል የተገኙ መንትዮች | | 11% |
| ከሁለት እንቁላል የተገኙ መንትዮች | | None! |

በዚህ ጥናት በአንድ እንቁላል መንትዮች መካከል የተዘገበው 11% መመሳሰል አስቀድሞ ቤይሊና ፒላርድ ከዘገቡት 52% እጅግ የራቀ መሆኑ ግልጽ ነው፡፡ እንዲሁም ሆኖ ይሄው ቁጥር (11%) በስታቲስቲክስ ከሚገመተው ከ 1-4% ግብረሰዶማዊነት ላቅ ያለ ሆኖ እናገኘዋለን፡፡ ሆኖም ግን አንድ አይነት መንትዮች እጅግ ተመሳሳይ በሆነ አስተዳደግና የአካባቢ ተጽእኖ እንደሚያልፉ ስናስብ ከሌሎች የተለየ መመሳሰል ቢታይባቸው የሚያስገርም አይሆንም፡፡

ቤይሊ፣ ዳን እና ማርቲን በጥናታቸው ዘገባ በግልጽ እንዳስቀመጡት፣ የእነርሱ ውጤት የሚያመለክተው የቀደመው የ 1991 የቤይሊና ፒላርድ ጥናት ውጤት በናሙና መዛባት ምክንያት ከመጠን በላይ መጋነኑን ነው፡፡ ከዚህም በተጨማሪ፣ ጥናቱ ግብረሰዶማዊነት የዘረ-መል ቅንብር (ጄነቲክ ኮዲንግ) ውጤት ላለመሆኑ ጠንካራ ማስረጃ ነው፡፡

እነዚህን ሁለት ጥናቶች እንደምሳሌ ወሰድን እንጂ፣ ሌሎች ብዙ ጥናቶችም በግብረሰዶማዊነት መነሻና የዘረ-መል መላምት ዙርያ ተካሂደዋል አሁንም በመካሄድ ላይ ናቸው፡፡ ከነዚህም ውስጥ፣ በአንጎል ይዞታ፣ በሆርሞን፣ በክሮሞዞምና ዲ.ኤን.ኤ ወዘተ ላይ ያተኮሩ ይገኙባቸዋል፡፡ ከጥናቶቹም አንዳንዶቹ ግብረሰዶማዊነት አብሮ የሚወለድ ነው የሚለውን መላምት የሚደግፍ ውጤት ይዘው ሲገኙ፣ ሌሎቹ ደግሞ ይሄንን የሚያፈርስ ውጤት ይዘው ቀርበዋል፡፡

ቀደም ሲል በምሳሌ እንዳየነው፣ በዘመናችን የግብረሰዶማዊነት አጀንዳ በሳይንስ መድረኮች ላይ ብዙ ደጋፊዎችና አራማጆች አግኝቶ ይታያል፡፡ ስለዚህም፣ አንዳንድ የምርምር ሥራዎች በግብረ ሰዶማውያን ደጋፊዎች ፖለቲካዊ አጀንዳ የሚመሩ ናቸው፡፡ ከዚህ የተነሳ በአሁኑ ጊዜ ሳይንሳዊ የምርምር ውጤቶች ብቅ

ሲሉ ውጤቱን አምኖ ከመቀበል በፊት ጥናቱ በማን እንደተካሄደ፣ እንዲሁም ከጀርባው የየትኞቹ ድርጅቶች የገንዘብ ድጋፍ እንዳለ መመርመር የግድ እየሆነ መጥቷል፡፡ ይሄውም ባለፉት አስርት-አመታት በሳይንሳዊ ጥናቶች ስም የተዛቡ ውጤቶች የመዘገባቸው አሳዛኝ ክስተት እየተበራከተ ስለመጣ ነው፡፡

- በማጠቃለያ ግን ሊሰመርበት የሚገባው ሳይንስ በሙሉ እርግጠኝነት ግብረሰዶማዊነት አብሮ የሚወለድ፣ ዘረ-መላዊ (ጄነቲክ) መነሻ አለው የሚል መደምደሚያ ፈጽሞ የሌለው መሆኑ ነው፡፡

## ግብረሰዶማዊነትን መቃወም ለምን አስፈለገን? የግብረሰዶማዊነት አደገኛነትና መዘዞቹ

በአሜሪካ ፋሚሊ ሪሰርች ኢንስቲትዩት ከተለያዩ ጥናቶች የተጠናቀረው ዘገባ ማየት እንደሚቻለው የግብረሰዶማውያን ባህሪያት በአለም ዓቀፍ ደረጃ አንድ ነው::

ጥናቶቹ አበክረው እንደሚያስገነዝቡት ግበረሰዶማዊ ባህሪይ ለብዙ ችግሮች የሚዳርግ በግለሰብና በሕብረተሰብ ላይ ብዙ ጣጣዎችን የሚያመጣ ነገር ነው:: ከዚህ ቀጥሎ በተለያዩ ጥናቶች ላይ ከቀረቡት ችግሮች ውስጥ ዋና ዋናዎቹን እንመለከታለን::

| የንጽጽሩ ዓነት | ግብረ ሰዶም(ሆሞሴክሹዋል) | ተቃራኒ-ጾታ (ሄትሮሴክሹዋል) |
|---|---|---|
| 1. አማካይ የዕድሜ ርዝመት | 55 አመት ለወንዶች | 75 አመት ለወንዶች |
| 2. ኤች አይ ቪ እና ሌሎች የአባለ ዘር በሽታዎች | ከፍተኛ(ከ5-64 እጥፍ) | አናሳ |
| 3. የጉበት የካንሰርና ሌሎች የጤና ችግሮች | ከፍተኛ | አናሳ |
| 4. የሥነ-ልቦና ችግር | ከፍተኛ | አናሳ |
| 5. ራስን የመግደል ወንጀል | ከፍተኛ (ወንዶች 35% ሴቶቹ 37%) | አናሳ (ወንዶች 11% ሴቶች 24%) |
| 6. ህጋዊ ያልሆኑ እጾችን መጠቀም | ከፍተኛ | አናሳ |
| 7. በግብረ-ስጋ ግንኙነት ላይ ያልተለመደ ትኩረት | ከፍተኛ | አናሳ |
| 8. በአንድ አለመወሰን | ከፍተኛ (ከ 4.5 እስከ 13 እጥፍ) | አናሳ |
| 9. በልጆች ላይ የሚደረግ የወሲባዊ ጥቃት | ከ >3 እስከ >10 | 1 |

| | | |
|---|---|---|
| ድግግሞሽ | | |
| 10. ተያያዥ ማህበራዊ ችግሮች | ከፍተኛ | አናሳ |

የግብረ-ሰዶማውያን ወንዶች የአኗኗር ዘይቤ ከግብረ-ገባዊና ከታማኝነት እሴት ገጽታው ባሻገር መሰረታዊ ችግሮቹ የተለያዩ ከተፈጥሮ ውጪ የሚደረጉ የግብረ-ሥጋ ግንኙነቶች ዓይነቶች ናቸው፡፡ በ RFSL ኦፊሴላዊ ድረ-ገጽ ላይም (‹‹አናል ማኑዋል››ማጣቀሻ 13) ይህ ልምምድ ማዕከላዊ የአኗኗር ዘይቤያቸው መሆኑንም በማስረጃነት ተጠቅሶአል፡፡ ከዚህ ዓይነት ልምምድም መነሻነት ተያያዥነት ያላቸው በርካታ የጤና ቸግሮችና መዘዞች ተከትለው ይከሰታሉ፡፡

1. አማካይ የዕድሜ ርዝመት




በአሜሪካ አገር ባሉ ወንዶች ላይ በቀረበ ስታቲስቲካዊ መረጃ እንደተመለከተውና በሌሎችም ጥናቶች እንደተደገፈው የወንድ ግብረ-ሰዶማውያን ከሌሎች ወንዶች ይልቅ እድሜያቸው በሃያ አመት ያጥራል። (ማጣቀሻ.1 (ሳይኮሎጂካል ሪፖርትስ (2005፤96፡693-697)ና ማጣቀሻ.2 (ኢንተሪም ጆርናል ኦፍ ኤፒደሞሎጂ 1997፡ ቮሊ.26፤657-61)

ይሄ ማለት ደግሞ ግብረሰዶማዊነት ሲጋራ ከማጨስ ይልቅ እጅግ የበለጠ አጥፊና እጾችን የመጠቀም ያህል አደገኛ ነገር ነው ማለት ነው።

በአሜሪካ በአስራሁለት አመት ውስጥ በታተሙ የግብረሰዶማውያን መጽሄት ላይ በቀረበ ስታትስቲክሳዊ መረጃ ግብረሰዶማውያን ሆነው ከሞቱ 6516 ሰዎች ውስጥ 98% የሚሆኑት የሽምግልና ዕድሜ ክልል ሳይደርሱ መሞታቸው ሲመዘገብ ከዚህ ውስጥ በኤድስ ምክንያት የሞቱት አማካይ ዕድሜ 39 ብቻ ነው። ከኤድስ በተለየ ምክንያት የሞቱት ግብረሰዶማውያን አማካይ ዕድሜ ደግሞ ለወንዶቹ 42ና ለሴቶቹ 44 መሆኑ ተዘግባል።

2. ኤች አይ ቪ እና ሌሎች የአባለ ዘር በሽታዎች

በግብረሰዶማውያን የሚዘወተሩ ወሲባዊ ግንኙነት ዓይነቶች ለተለያዩ የአባለዘር በሽታዎች እንደሚዳርጉና በሕብረተሰብም መሃከል ለበሽታዎቹ መሰራጨት እጅግ ከፍተኛ አስተዋጽኦ እንደሚያደርጉ በተለያዩ ጥናቶች ላይ የቀረበ ጉዳይ ነው። ኤድስ፣ ሄፒታይተስና የካንሰር በሽታን ጨምሮ አንዳንዶቹ በሽታዎች በሌላው ሕብረተሰብ እንኳን የማይታወቁ መሆናቸው ተመልክቶአል።

ጸያፍ በሆነ መንገድ በሰገራ መውጫ በኩል የሚደረገው የግብረ-ሥጋ ግንኙነት በግብረ-ሰዶማውያን ወንዶች ዘንድ ዋንኛ የፍትወት መንገድ መሆኑን በግብረሰዶማዊነት አራማጅነቱ በሚታወቀው በRFSL ድረ-ገጽ ላይ የቀረበው ‹‹ኣነል ማኑዋል›› በግልጽ ያወጣው ጉዳይ ሲሆን (ማጣቀሻ.14) የዚህ ልምምድ ድግግሞሽ ደግሞ እ.ኤ.አ ከ1994-1997 ባሉት ዓመታት ውስጥ ብቻ ከ57.6% ወደ 61.2 % ማሻቀቡን በአሜሪካን ፋሚሊ ሪሰርች ኢንስቲትዩት የቀረቡ ጥናቶች ይገልጣሉ፡፡

በተለይም በኒው ኢንግላንድ ጆርናል ኦፍ ሜዲሲን በቀረበ ጥናት ላይ እንደተመለከተው - ጸያፍ በሆነ ሁኔታ በሰገራ መውጫ በኩል የሚደረገው ዋንኛው የግብረሰዶማውያን የግብረ-ሥጋ ግንኙነት መንገድ ከመደበኛው የተቃራኒ ጾታ የግብረ-ሥጋ ግንኙነት ይልቅ ከ5-64 እጥፍ በላይ ለአባለ-ዘር በሽታዎች ጥቃት የተጋለጠና በከፍተኛ ደረጃ ለበሽታዎቹ መተላለፊያ መንገድ ነው፡፡

ይህንን ያውቁ ኖሯል?

የኤች.አይ.ቪ. በሽታ ለመጀመሪያ ጊዜ የተመዘገበው እ.ኤ.አ. በ1981 በኒውዮርክና የግብረ-ሰዶማውያን ክለቦች ውስጥ ሲኖን የመጀመሪያ የበሽታው መጠሪያ ጌይ ሪሌትድ ኢሚዩን ዲስ ኦርደር ( ጂ.አር.አይ.ዲ.) የሚባል ነበር፡፡ ግን ውሎም ሳያድር የግብረ-ሰዶማውያኑ ማህበረ-ሰብ ተጽእኖ ማሳደር በመቻላቸው የበሽታው መጠሪያ ኤ.አይ.ዲ.ኤስ.(ኤይድስ) ማለትም የተፈጥሮ መከላከያ አቅምን የሚጎዳ ሲንድሮም እንዲባል ሆነ፡፡

ከኤች.አይ.ቪ ኤድስ ባሻገር በርካታ በግብረ-ስጋ ግንኙነት የሚተላለፉ በሽታዎች አሉ፡፡ ከእነርሱም መካከል በውስጡ 70 የተለያዩ ቫይረሶችን በመያዙ በበሽታ መጠሪያነቱ የሚታወቀው ሂዩማን ፓፒሎማ ቫይረስ (ኤች.ፒ.ቪ) ይገኝበታል፡፡

መጽሐፍ ቅዱስ በሮሜ 1፡27 ግብረሰዶማዊነትን ስለሚለማመዱ ሰዎች ሲናገር "በስሕተታቸው የሚገባውን ብድራት በራሳቸው ተቀበሉ" የሚለው ከዚህ ጋር ስምም ሆኖ እናገኘዋለን።

## 3. የጉበት የካንሰርና ሌሎች የጤና ችግሮች

ግብረ-ሰዶማውያን በዋናነት የሚለማመዱት ወሲባዊ ግንኙነት የውስጥ ሰውነትን የሚሸፍነውን ስስ አካል በመጉዳት በደም ዝውውር ውስጥ ባክቴሪያ እንዲተላለፍ በማድረግ የፊንጢጣ ካንሰርን ያመጣል፡፡ በተጨማሪም በፈሳሽ መልክ ወደ ደም ዝውውር በሚገባ ፈሳሽ ምክንያት ለጉበት በሽታ ና ባሁኑ ጊዜ የ‹‹ጌይ ቦውል ሴንድሮም›› በመባል እስከ መታወቅ ለደረሰውና ተያዢነትም ላላቸው እጅግ በጣም አደገኛ ለሆኑና እንደ ሽጌሎሲስ፣ጋርዲያ ላምብሊያ፣ ለመሳሰሉት ላልተለመዱ ሌሎች በሽታዎች ሰለባዎች ይሆናሉ፡፡

ለእነዚህና ለሌሎችም በግብረሰዶማዊነት ለሚዛመቱ በሽታዎች ደግሞ ትልቁን አስተዋጽኦ ከሚያደርጉት ነገሮች መሃል በግብረሰዶማውያን መሃከል የተለመደው እጅግ ልቅ የሆነና ከተፈጥሮአዊ ሥርአት ውጪ የሆነው ወሲባዊ ልምምዳቸው ዋንኛው ሲሆን በአንድ ያለመወሰን (Promiscuity) ባህርይ ደግሞ ሌላው ተጠቃሽ ነገር ነው።

በኤፍ.ኤን ጁድሰን በፍብሩዋሪ 1984 በዩሮሎጅ ክሊኒክስ ኦፍ ኖርዝ አሜሪካ 11 ቁጥር 1 በተጻፈ አንድ ጽሁፍ ላይ ግብረ-ሰዶማውያን ወንዶች ከፍተኛ ቁጥር ካላቸው ሰዎች ጋር በመገናኘታቸውና በሚለማመዱአቸው ኢ-ተፈጥሮአዊ ግብረ-ስጋ ግንኙነት መንገዶቻቸው እንደ ጉበት በሽታ፣ጀርዲያ፣አሜባ፣ ሺግሎሺሽ፣ካመሎባክ፣አኑሬክታላ፣ ጨብጥ፣ ክልሚዲያ ትኮማቲስ፣ትሬፖኔ ፓላዲም ና ሂዩማን ፓፒሎማ ቫይረስ በመሳሰሉ በሽታዎች መለከፋቸው እድል ከፍተኛ መሆኑ ተጽፎአል፡፡

## 4. የሥነ-ልቦና ችግሮቹ

በታሪክ እንደሚታወቀው ከስነ-አእምሮ ምርመራዎችና የአሃዝ መምሪያ ጽሁፍ ላይ ግብረሰዶማዊነት እስከ 1973 ድረስ እንደ ስነ-አእምሮ በሽታና ልክ እንዳልሆነ ባሕሪይ ይታይ ነበር። በፖለቲካዊ ግፊት ምክንያት ግን ከመምሪያው ጽሁፍ እንዲወጣ ተደርጉአል።

ይሁን እንጂ ዛሬም በግብረሰዶማውያኑ ላይ የሚታዩት እንግዳ ባሕሪያት ግጭት የሞላባቸው፣ ልቅና እድሜ የሚያሳጥሩ በመሆናቸው የአእምሮ በሽታ መሆኑን የሚያመለክቱ ናቸው።
በግብረሰዶማውያን ሥነ-ልቦና ላይ ሰፊና ብዙ ጥናቶችን በማድረግ ታዋቂ የሆኑት ዶ/ር ኤርቪን ቢየር ግብረሰዶማውያንን ሲገልጹ "ቁጠኞች መራርና ዝቅተኛ የሃላፊነት ስሜት ያላቸው" ይሉአቸዋል።*(2)*
እዚህ ጋ ሊሰመርበት የሚገባው ነገር ብዙ ጊዜ በግብረሰዶማዊነት አራማጆች እንደሚባለው  ግብረሰዶማውያን ለሥነ-ልቦና ችግር የሚጋለጡት ያለአግባብ በሌላው ሕዝብ ስለሚገለሉ ሳይሆን እኚህ ሊቅም እንደሚሉት ከምርጫቸውና ከግብረሰዶማዊ ልምምዳቸው የተነሳ በሚሆነው ሥነ ልቦና ለውጥ የተነሳ ነው:: እንደእሳቸው አባባል ግብረሰዶማዊነት አጭር፣ ብቸኝነት የሚያጠቃው፣ ምንዝር የበዛበት፣ ዋስትና የሌለው፣ በበሽታና በአደጋ የተሞላ ነው:: ምንም እንኳን ግብረሰዶማውያን  የታሰሩት በራሳቸው የፍትወት ሱስ ቢሆንም የሥነ አእምሮ ችግሮቻቸው ሲታዩ ግን በሞት እስር ቤት በቀጥታ የሚያመሳስሏቸው ናቸው::

## 5. ራስን የመግደል ወንጀል

በርካታ ራስን በራስ የማጥፋቱ ድርጊት ጎልቶ የሚታየው እያደገ በሚሄደው ግብረ-ሰዶማዊነት ምክንያት ትግል ላይ ያሉ ወጣቶች ወንዶች መካካል ሲሆን ምክንያቱም በሚያሳዝን መልኩ ትክክለኛ የወንድነት ጾታ ግንዛቤ ላይ እንዲደርሱ የሚረዳቸውን ምክርም ሆነ ድጋፍ ለማግኘት አለመታደላቸው ነው፡፡ ተሞክረው በከሸፉ ራስን በራስ የማጥፋት ድርጊቶች ላይ የተለያዩ ድጥናቶች ተካሂደዋል ፡፡ ሁሉም ጥናቶች በጥቅሉ የሚያመለክቱት በታዳጊ ግብረ-ሰዶማውያን ወጣት ወንዶች ና ሴቶች መካካል ከፍተኛ ደረጃ ላይ የደረሰ ራስን በራስ የማጥፋት ሙከራ መደረጉን ነው፡፡ ከእንደዚህ መሰሉ የግብረ-ሰዶማውያን ራስን በራስ የማጥፋትድ እርምጃ በስተጀርባ እንደ መነሻነት የሚቆጠሩ ምክንያቶች መካከል  መገለል አንዱ ሲሆን ሌላው ተጠቃሽ ምክንያት ግን በግብረ-ሰደማዊነቱ ልምምድ ስር እየሰደደ ና የኑሮው ስርዓት እያደረገው ሲሄድ ድርጊቱ ፈጽሞ ወደ እውነተኛው እርካታ ሊያደርሰው እንደማይችል ይገነዘባል፡፡ የትናንቱ ድርጊቱ ለዛሬው እርካታን ባልሰጠው መጠን እርካታን ፍለጋ ለይቶለት ሌሎች አስነዋሪ ልምምዶች ውስጥ በመግባት ጭራሽ ወዳልታሰበ ያለመርካት ውስጥ ይገባል፡፡ ይሄ የሚነግረን ግብረ-ሰዶማዊነት ያልተቆጠበ ና ሙሉ ተቀባይነትን ካገኘ በግብረ-ሰዶማውያን መካከል የሚታየው ራስን በራስ የማጥፋቱ እርምጃ ሊቀንስ ይችላል የሚለው ግብረ-ሰዶማውያን የሚያራምዱት ፕሮፖጋንዳ የተሳሳተ መሆኑን ነው ፡፡

በሌላ ጥናት እንደተመለከተው ከግብረሰዶማውያን ወንዶች 35% (በአንጻሩ ግብረሰዶማውያን ያልሆኑ ወንዶች 11%) እና ከሴቶቹ 37% (በአንጻሩ ግብረሰዶማውያን

ያልሆኑ ሴቶች 24%) ራሳቸውን ለማጥፋት ከልብ አስበዋል ወይንም ሙከራ አድርገዋል።

## 6. ህጋዊ ያልሆኑ እጾችን መጠቀም

በህግ ያልተፈቀደ ዕጾችን መጠቀም በግብረ-ሰዶማውያን ዘንድ ያለውን ቦታ ለመገንዘብ ከፈለግን ወደ RFSL ድረ-ገጽ መሄድና መመልከት ያስፈልገናል፡፡ በስዊድን ግብረ-ሰዶማውያንን በሚወክለው RFSL ተብሎ የሚጠራ ተቋም ድረ-ገጽ ላይ በህግ እንካን ያልተፈቀዱ እጾችን ዝርዝሮችንና የእያንዳንዱን እጽ የአጠቃቀም ዝርዝር ጭምር በግልጽ ተጽፎ ይገኛል፡፡ እዚህ ጋር « በግብረ-ሰዶማውያን ና በህገ-ወጥ ዕጾች መካከል ለምን ጠንካራ ትሰስር ይታያል? » ብለን መጠየቅ ተገቢ ይሆናል።
ለዚህ ጥያቄ መልስ ለማግኘት ርቀን ሳንሄድ በዚሁ ድርጅት RFSL ድረ-ገጽ ላይ በአራማጆቹ በራሳቸው ቃላት እንዲህ ተብሎ ተጽፎ የሚገኘውን መመልከት በቂ ይሆናል፡-
“ሪሚንግ..
ወደ ልምምዱ ውስጥ ሳልገባ ሰው ና ለመጀመሪያ ጊዜ ለሚለማማደው
ሰው … (የግብረሰዶማዊ የግብረ ስጋ ግንኙነት ተጠቅሶ) ሚስጢራዊና ሥቃይ የሚያስከትል ና ጭራሹንም የሚያስጠላ ድርጊት ነው፡፡ ይሁን እንጅ ልምዱ ላላው ሰው ግን የምድር ላይ ገነት ይሆንለታል፡፡…
ይህ አባባል በእርግጥም የሚያመለክተው እንደዚህ ያሉ አስደንጋጭ ድርጊቶች ውስጥ ለመግባት ህጋዊ ያልሆኑ እጾችን መጠቀም ምቹ ሁኔታን ለመፍጠር እንደሆነ ነው፡፡

## 7. በግብረ-ስጋ ግኝኙነት ላይ ያልተለመደ ትኩረት

ለግብረ-ሰዶማዊው ሰው ባጠቃላይ የህይወቱ አብዛኛው ክፍል የተያዘው በጾታ ግንኙነት ለይ ነው፡፡ ለአቅመ-አዳም የደረሰ ና በጾታ-ግንዛቤው ረገድ ሁለቱንም ሃሳቦች የተረዳና በጾታዊ ፍላጎቱ ንቁ የሆነ ሰው ዓይነተኛ ና ከፍተኛ የሆነ የግንኙነት ፍላጎት ውስጥ ይገባል፡፡ እንዲህ ዓይነቱ ሁኔታ በተቃራኒ-ጾታ ፍላጎት ውስጥ ላለ ሰው ወደ ጋብቻ ና ቤተሰብ ወደ መመስረቱ እንዲያዘነብል ሲያደርገው ለግብረ-ሰዶማዊ ሰው ደግሞ የልምምዱ መጠንና ስፋቱ ከተፈጥሮ ውጭ ይሆንበታል፡፡ በስዊድን አገር በሚደረገው « ጌይ ፓሬድ» በዓል ላይ ግብረ-ሰዶማውያን በንጉሱ ቤተ መንግስት ፊት ሳይቀር በአደባባዮች የሚያሳዩት በወሲባዊ እንቅስቃሴ የተሞላ አጸያፊ ትእይንት ይህንኑ በጉልህ የሚያንጸባርቅ ነው፡፡

እስከ አሁን ያነሳናቸውን ብቻ በመመልከት ምናልባት ግብረሰዶማዊ ሕይወት የግለሰቡ ጉዳይ እንጂ ማህበራዊ ጉዳይ ተደርጎ መታየት ለምን አስፈለገው ብሎ ለሚጠይቅ በቂ መልስ ማቅረብ አይቻል ይሆናል:: ከዚህ ቀጥሎ በምንመለከታቸው ሃሳቦች ግን የግብረሰዶም ሕይወትን ማህበራዊ ገጽታ ለማየት እንሞክራለን::

## 8. በአንድ አለመወሰን / ብዙ የወሲብ አጋር መያዝ

ምንጩን ጠቅሶ በሮን የቀረበው ጥናታዊ ጽሁፍ ላይ እንደቀረበው
በስዊድን በህይወት ዘመን ውስጥ አጋር (ፓርትነር) በማፍራት ግብረ-ሰዶማውያን በሆኑ ወንዶች መካካል የሚታየው ጓደኛነት ብዛት አማካይ ቁጥር በህይወት ዘመን ውስጥ 50 ሲሆን በሌሎቹ ወንዶች መካከል የሚታየው የጓደኝነት ብዛት ግን 4 ብቻ ነው፡፡

በአውስትራሊያ በተደረገ ጥናት ግብረሰዶማውያን ሴቶች ከሌሎች ሴቶች ይልቅ በሕይወት ዘመናቸው ከ50 በላይ የወንድ ወሲባዊ አጋር በመያዝ 4.5 እጥፍ ሪከርድ እንዳላቸው ተዘግቦአል።

በ1978 የተደረገ አንድ ጥናታዊ ጽሁፍን ጠቅሶ በአሜሪካን ፋሚሊ ሪሰርች ኢንስቲትዩት የቀረበው ሪፖርት እንደዘገበው ደግሞ ጥናቱ ከተደረገባቸው ነጭ ግብረሰዶማውያን ወንዶች መሃከል 75% በላይ የሚሆኑት ከ100 በላይ የወንድ ወሲባዊ አጋር በሕይወታቸው ዘመን እንደነበራቸው ሲያምኑ፣ 15% የሚሆኑት ደግሞ ከ250-499 አጋር እንዲሁም 28% የሚሆኑት ከ1000 ያላነሰ የወንድ ወሲባዊ አጋር እንደነበራቸው ተናግረዋል።

እንግዲህ ይህ አይነቱ የልቅነት ባሕሪይ ደግሞ በተለይም እንደ ኤችአቪ ኤድስ ያሉ በሽታዎችን ከማሰራጨት ጀምሮ በሕብረተሰብ ውስጥ ሊያደርስ የሚችለው ጉዳት ምን ያህል የከፋ እንደሆነ መገመት አያዳግትም::

## 9. በልጆች ላይ የሚደረግ የወሲባዊ ጥቃት ድግግሞሽ

በልጆች ላይ ወሲባዊ ጥቃት ወንጀል ድግግሞሽና መጠን በግብረ-ሰዶማውያን ወንዶች የተፈጸመው ከተለመደው ቁጥር በእጅጉ የላቀ ነው፡ ምናልባትም ቢያንስ በ3 ወይንም በአስር እጅ:: ከሌሎች ምንጮች ያገኘናቸው መረጃዎችም ይህንኑ የሚያጠናክሩ ናቸው::

ሀ) RFSL በራሳቸው ድረ-ገጽ ላይ በእድሜ የገፉ ወንዶች ከወጣት ወንዶች ጋር ስለሚያደርጉት የግብረ-ሥጋ ግንኙነት ልምምድ ያላቸውን አድናቆት ገልጠዋል፡፡ (ቁጥር.2)
ለ) ልጆችን በወሲባዊ ስራ ዘርፍ በማሰማራት በዓለማችን የምትታወቀው ታይላንድ በግብረ-ሰዶማውያን ጎብኝዎች ዘንድ ተመራጭ የጉብኝት ስፍራ የሆነችበት ምክንያት ምስጢር ያልሆነበትም ለዚህ ነው፡፡ በግብረ-ሰዶማውያን ወንዶች ላይ ባነጣጠረው በዚህ ዘገባ (ማጣቀሻ.8) አገሪቱ ለምን ተመራጭብ እንደሆነች ተጽፏል፡፡
« ስለ ግብረ-ሰዶማውያኑ ሁኔታ»
የግብረ-ሰዶማውያን ማህበረ-ሰብ ጉብኝታችሁን በተቻለ መጠን አስደሳች እንዲሆን እንሻለን፣ እንመኛለን፡፡
...እኛ እንደ ምዕራባውያን ግብረ-ሰዶሞች ቀዳሚ ና የዘወትር ፍላጎታችን የፍትወት እርካታን ነው፡፡ ከድርጊቱ ጋር ተካፋይ ሆኑም ወይም አልሆኑም እዚህ አገር በግብረ-ሰዶማውያኑ ማህበረ-ሰብ መካከል ቆይታዎን የሚመች የሚያደርገው እንዲህ ዓይነት ግንዛቤ ሲኖርዎት ነው፡፡ የዚህ አገር የእረፍት ጊዜ ቆይታዎ መልካም እንዲሆን እየተመኘን... »

ሐ) ኔዘርላንድና ቤልጂየም ታዳጊ ልጆች ለጋብቻ ወይንም ለግብረ-ስጋ ግንኙነት መድረሳቸውን የሚያረጋግጠውን የህግ አማካይ እድሜ ወደ 12 ዓመት በተደጋጋጋሚ ዝቅ በማድረግ እርምጃቸው ይታወቃሉ፡፡

«ሳይኪያትሪ ጆርናል ኦፍ ዘ ዩኒቨርሲቲ ኦፍ ኦታዋ» በተባለ ጆርናል ላይ የቀረበ አንድ ሪፖርት ( ማጣቀሻ.10) ከጠቅላላው ለአቅመ-አዳም/ሄዋን ያልደረሱ ልጆችን ለፍትወታዊ ግንኙነት የመድፈር ወንጀል ሪፖርት ውስጥ ከ19%-33% የሚሆኑት በግብረ-ሰዶማውያን

ወንዶች የተፈጸሙ መሆናቸውን ደርሰውበታል፡፡ ከጠቅላለው ወንዶች 3% ብቻ ግብረ-ሰዶማያን በሆኑበት ሁኔታ ውስጥ ልጆችን ለፍትወታዊ ግንኙነት የመድፈሩ መጠን ግብረ-ሰዶማውያን ካልሆኑት ሰዎች ይልቅ በግብረ-ሰዶማውያኑ ከ6 (19/3)እስከ 11(33/3) እጅ ተደጋጋሚ እንደሆነ ያሳያል፡፡

ሌሎችም ተቀባይነት ያላቸው ጥናቶችና ሪፖርቶችም ሁሉ ልጆችን ለወሲባዊ ጥቃት የመድፈሩ ልማድ (ፔዶፊሊያ) ድግግሞሽ በኅላ ሁኔታ የሚታየው በግብረ-ሰዶማውያን ወንዶች መካከል መሆኑን በግልጽ በሚያሳዩበትና  ይህ አይነቱም ጥቃት በከፍተኛ ሁኔታ እየጨመረ መሄዱ እየታወቀ የስዊድን ፓርላማን ጨምሮ አንዳንድ ምዕራባውያን አገሮች ግብረ-ሰዶማውያን ጓደኛሞች ልጆችን በጉዲፈቻነት እንዲያሳድጉ ፈቃድ መስጠታቸው አሳፋሪና የችግሩን እያየለ መምጣት ያመላክታል ፡፡

## 10.ተያያዥ ማህበራዊ ችግሮች

ጽድቅ ሕዝብን (nation) ከፍ ከፍ ታደርጋለች፤ ኃጢአት ግን ሕዝብን ታስነውራለች። ምሳሌ 14:34

የግብረ-ሰዶማውያን ማህበረ-ሰብ የህክምና፣የማህበራዊና፣የፋይናንስ ሃብቱን እጅግ በሚጎዳ መልኩ ከፍተኛ ወጪ ይዳርጋል:: ለምሳሌ በስዊድን ለኤች.አይ.ቪ. ኤይድስና፣ በአደንዛዥ-እጽ ሱስ ለተለከፉና ለአባለ-ዘር በሽታዎች የሚወጣው ወጪ ለሌሎች ማህበራዊ አገልግሎቶች ና ለምርምር ስራዎች የተመደበውን ሃብት እንዲቀንስ አድርጎታል፡፡

ከሚያስከትለው የሥነ ልቦና ችግር ትይዩ:
ከ1ሺህ በላይ ግብረሰዶማውያንን የማከም ልምድ ያላቸው ዶ/ር ኤድሞንድ በርግለር እንደሚያስቀምጡት ግብረሰዶማውያን ብዙውን ጊዜ ራሳቸውን ጎድተው ዞረው በሌሎች ምክንያት እንደተጎዱና ፍትህ እንደተዛባ ወይንም እንደሌለ የማቅረብ አዝማሚያ አላቸው። በዚህም

- ራስን በመከላከል ሰበብ በሌሎች ላይ ጥላቻን የመንዛት
- ከልክ ያለፈ ራስ ወዳድነትና ሌላውን የመናቅ ችግር ያለባቸው
- በውስጣቸው ያለውን ጥፋተኝነት ስሜትና ጭንቀት ለመሸፈን ሁኔታዎችን የማናናቅ ዝንባሌ  የሚታይባቸው
- በሕብረተሰብ  ተቀባይነት  ያላቸውን  ሌሎች  ግብረገባዊ  መለኪያዎችንና  ሕጎችን የማይቀበሉ
- ብዙውን ጊዜም አመኔታ ሊጣልባቸው የማይችል ሆነው እናገኛቸዋለን::

ከ5 ትልልቅ የአሜሪካ ከተሞች የተውጣጡ 4,340 ሰዎችን ባካተተውና ግብረሰዶማውያንን ከሌላው (ማለትም ከሄትሮሴክሽዋሎች) ባነጻጸረው ሰፊ ጥናት ግብረሰዶማዊነት ግንኙነትን ልል እንደሚያደርግ ተገልጿል:: ውጤቱ እንዳሳየው:

- ወደ ጋብቻ የመጡ ግብረሰዶማውያን ካሉት 50% ብቻ ናቸው
- ያገቡትም ከሌላው ይልቅ በማመንዘር 3 እጥፍ ሪከርድ አላቸው!
- ለአጋሮቻቸው በታማኝነት በመቆየት ግብረሰዶማውያን ከ1 ዓመት ያነሰ ቆይታ ሲኖራቸው በአንጻሩ ግን ግብረሰዶማዊ ያለሆኑት ከ5 እስከ 10 ዓመት እድሜ ታማኝነት አላቸው::

- በትዳርም በመጽናት ተመሳይ ውጤት ተገኝቷል፤ ግብረሰዶማውያን ጥምር በአማካይ ሶስት ዓመት ሲቆዩ ግብረሰዶማዊ ያለሆኑት ግን በአማካይ 10 ዓመት ይቆያሉ:: (14)

# ግብረሰዶማዊነትን በተመለከተ በምእራባውያን አገሮች የሚታየው የግብረገብ ዝቅጠት፤

**ግብረሰዶምን በተመለከተ አሳዛኝና ዘግናኝ ነገሮች በስዊድን ይታያሉ። ከእነዚህም መካከል ጥቂቶችን ነገሮች ብቻ ለናሙና ከዚህ በታች ብንገልጽም እስካሁን ድረስ በየጊዜው የሚከሰቱ አሳዛኝ ክስተቶች እንዳሉ በዚህ አጋጣሚ ለአድማጮች ልንገልጽ እንወዳለን።**

የግብረሰዶም መንፈስ ምንያህል በምእራባውያን አገሮች ስር እንደሰደደና በሕብረተሰብ ውስጥ ምን ያህል እንደተስፋፋ ከሚያሳዩ ድርጊቶች መካከል በአብነት ተጠቃሽ የሆኑትን አንዳንድ ክስተቶች ከዚህ ቀጥሎ እናነሳለን።

- ግብረሰዶማውያን ላለፉት ተዳጋጋሚ ዓመታት መላ ከተማውን በአመት አንድ ጊዜ እየዞሩ እርቃናቸውን ወይንም ጥቂት ልብስ ብቻ አድርገው እየታዩ ነውራቸውን በአደባባይ ማስተዋወቅ ተፈቅዶላቸው በህጻናት፣ በአዛውንት ሁሉ ፊት ይህ ቅሌት ይካሄዳል!
- በግብረሰዶማውያንን የቅሌት ሰልፍ ፖለቲከኞችና ታዋቂ ሰዎች እየተገኙ ንግግር ያደርጋሉ፣ ድጋፋቸውን ይገልጻሉ።
- <<ክብራቸው በነውራቸው ነው>>...
- በሕዝብ የገቢ ቀረጥ የሚተዳደረውና የሚደገፈው የስዊድን ዋና ቴሌቪዥን የግብረሰዶማውያንን አጀንዳና ውሸታቸውን ለመንዛት እራሱን ፍጹም ያቀረበ እንደመሆኑ ጽንፈታዊና በጣም የሚገርመው ሚዛን የለሽ ፕሮግራሞች ለመላው የስዊድን ሕዝብ በተደጋጋሚ ሲቀርብ ይታያል። ለጽንፈታዊነቱ ግልጽ በሆነ ሁኔታ እንደ ማስረጃ ተጠቃሽ ከሚሆኑ ክንዋኔዎች አንዱ ከዚህ ቀደም ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስን የሚሳደብና ቤተክርስቲያኖችን ሁሉ እጅግ ያነጋገረና ያስቆጣ የፎቶ ኤግዚቢሽን ያቀረበችውን ያቺኑ ግብረሰዶማዊት ሴት የፕሮግራም መሪ አድርጎ ቀጥሮ ስለ ግብረሰዶም ጉዳይ ቃል ምልልስን እንድታካሂድ አስቀምጧታል።
- መገናኛ ብዙሃን ፍጹም ለግብረሰዶማውያን አጀንዳ የተሰጠ ነው። ስለዚህም ግብረሰዶማውያን ፕሮፓጋንዳቸውን ያላንዳች ተቃውሞ በመገናኛ ብዙሃን ይነዛሉ፣ የሕዝብንም አእምሮ በፕሮፓጋንዳ ቀስ በቀስ የማጠብን ስራ እያካሄዱ ይገኛሉ።
- ከቅርብ አመታት ወዲህ በተለይ በሆሊውድ ግብረሰዶማዊነት ተቀባይነትን እንዲያገኝ እየተሰሩ የሚቀርቡ ፊልሞች ለዚህ ተጠቃሽ ናቸው።
- በስዊድን ቴሌቪዥን ድረ ገጽ ላይ በተደረገ መጠነኛ አሰሳ በአንድ ሳምንት ውስጥ ብቻ ከ100 በላይ ስለግብረሰዶማዊነት ጉዳይ በአንድም በሌላም መንገድ የሚያነሱ ፊልሞችና ፕሮግራሞች ተዘርዝረው መታየታቸው የቴሌቪዥን ጣቢያው እራሱን ምን ያህል እንዳቀረበ ግልጽ ማስረጃ ነው።

- የግብረሰዶማዊነት አራማጅ ድርጅቶች በመንግስት ድጎማ እየተደረገላቸው በየትምሕርት ቤቱ እየዞሩ ግብረሰዶማዊነት ምንም ከሌላው የማይለይ (ኖርማል) ነገር እንደሆነ ያስተምራሉ። ግብረሰዶማዊነት ተፈጥሮአዊ አይደለም ብሎ የሚናገር ማንኛውም ሰው ግን ደግመኛ በትምህርት ቤት እንዳይገኝ የግብረሰዶማዊነት አራጃድ ድርጅቶች ተጽእኖ ያደርጋሉ፤ መንግስትና ትምሕርት ሚኒስቴርም ይተባበራቸዋል።
- እ. ኤ. አ. በጁላይ 2003 ዓ.ም. መጽሐፍ ቅዱስን መሰረት አድርገውና ጠቅሰው ግብረሰዶማዊነት ፍጹም ከተፈጥሮ ውጪ የሆነ ነገር እንደሆነ ሲያስተምሩ የተገኙ አንድ ኦከ ግሪን የተባሉ የ63 ዓመት የእግዚአብሔር አገልጋይ (መጋቢ) በአንድ የግብረሰዶማዊነት አራማጅ ተከሰዋል። ክሱም <<ግብረሰዶማውያንን ነቅፈው በማስተማራቸው ጥላቻ ነዝተውብናል>> የሚል ነበረ። የስዊድን የመጀመሪያ ፍርድ ቤትም እኚሁ አገልጋይ የሰበኩትን ስብከት ከሰማ በኋላ የአንድ ወር እስራት ፈርዶባቸዋል። እኚህ አገልጋይ ግን ተስፋ ባለመቁረጥ በቅድሚያ ለይግባኝ ፍርድ ቤት ይግባኝ ብለው በዲሞክራሲያዊ ሕብረተሰብ ያለው የሃይማኖትና የንግግር ነጻነት ይሄንን እንዲሉ እንደሚፈቅድላቸው ገልጸው ቢከራከሩ ጉዳዩ እስከ ከፍተኛው ፍርድ ቤት ድረስ ደርሶ በብዙ ጭንቅ ነጻ ተለቀዋል።

# በስዊድን የሉተራን ቤተክርስቲያን የሚታየው አሳዛኝ ገጽታ፤

እ.አ.አ. በ1998 ዓ.ም. ሴፕቴምበር 19 ቀን በስዊድን ሃገር በኡፕሳላ ከተማ የስዊድን የሉተራዊት ቤተክርስቲያን ዋና አጥቢያ ተደርጎ በሚታሰበው ዱም ሺርካን ተብሎ በሚጠራው ቤተክርስቲያን እጅግ አሳዛኝና እስከዛሬም ጠባሳው ያልጠፋ ክፉ ነገር ተከናወነ። ይህም በዚያች ቤተክርስቲያን ዋና ሃላፊ ፈቃድና ትብብር ጌታችንና አምላካችንን ኢየሱስ ክርስቶስን እንደ ግብረሰዶም የሚያቀርብ <<ኤከ ሆሞ>> የሚባል እግዚብሔርን የሚሳደብ የፎቶ ኤግዚቢሽን እንዲታይ ተፈቅዶ ታይቷል። ይሄንን የፎቶ ኤግዚቢሽን እንዳይካሔድ የተቃውሙ ሰዎችና ቤተክርስቲያኖች ምንም ተሰሚነት አላገኙም። ኮጌ ሃማር የተባለው ከዚህ ቀደም የስዊድን ቤተክርስቲያን ጳጳስ የነበረው ሰው ለዚህ የፎቶ ኤግዚቢሽን ፈቃድ የመስጠቱን እርምጃ ደግፎታል።

- ኤኬ ሆሞ የተባለውን ይሄንኑ የፎቶ ኤግዚቢሽን ያቀረበችው ግብረሰዶማዊ ሴት በቅርብ ጊዜ “In Hate we trust” (በጥላቻ እንታመናለን) በሚል ርእስ ግብረሰዶማዊነትን የማይቀበሉ ክርስቲያኖች ጥላቻን የተሞሉ አድርጎ የሚያቀርብ ሌላ የፎቶ ኤግዚቢሽን አቅርባለች።
- የስዊድን ሉተራን ቤተክርስቲያን ዋና ጳጳስ የነበረው ኮጌ ሃማር የተባለው ሰው ግብረሰዶማዊነትን በስዊድን ቤተክርስቲያንና በሕብረተሰቡም ውስጥ በከፍተኛ ደረጃ ማራመዱ ሳያንሰው በግብረሰዶማውያን የቅሌት ሰልፍ ላይ የክብር እንግዳ ሆኖ ቀርቦ ንግግር አድርጓል። <<Samhället har utvecklats snabbare än kyrkan>> ሕብረተሰብ ከቤተክርስቲያን ይልቅ ፈጥኖ አድጎአል ብሎ በመናገር ሕብረተሰብ ውስጥ የሚካሄደውን የሞራል መበስበስ ቤተክርስቲያን እንድታቅፈውና እንድትቀበለውም ለማድረግ የዲያቢሎስን አጀንዳ በቤተክርስቲያን ካራመዱ ግለሰቦች በአብነት ተጠቃሽ የሚሆን ሰው ነው።
- እራሱ ግብረሶዶማዊ የሆነውንና ክርስቲያኖችንና እውነተኛ አማኞችን በንግግሩ፤ በጽሁፉና በዘፈኑ እጅግ አድርጎ የሚነቅፍና የሚያናቋሽሸውን አንድ ዮናስ

ጋርዴል የተባለውን ተሳዳቢ አርቲስት የሉንድ የቲዎሎጂ ኢንስቲትዩት የክብር ዶክትሬት ሸልሞታል። *<<በረዶ በበጋ ዝናብም በመከር እንዳይገባ፥ እንዲሁ ለሰነፍ ክብር አይገባውም።>> መጽሐፈ ምሳሌ* 26፤1

- ኦክቶበር 27 2005 የስዊድን ሉተራን ቤተክርስቲያን (ስቬንስካ ሺርካን) ግብረሰዶማውያንን ጋብቻን የመሰለ ስርዓት ልታካሂድላቸውና በቤተክርስቲያን ውስጥ ለግንኙነታቸውና ለፍቅራቸው <<ባርኮት>> ልታካሂድላቸው ወስና ይሄንን ማድረግ ጀምራለች።
- ግብረሰዶም የሆኑ ቀሳውስት ትልቅ ስፍራ ተሰጥቶአቸው ግብረሰዶማዊነትን በቤተክርስቲያን በማስፋፋትና ተቀባይነት እንዲያገኝ በመስራት ላይ ይገኛሉ። ላርሽ ጎርድፌልት የተባለው ግብረሰዶም ቄስ በግብረሰዶም ጉዳይ የሉተራን ቤተክርስቲያን ሊኖራት ስለሚገባው አቋም ስትወያይ ከነበሩት የግብረሰዶማዊነት አራማጆች አንዱ ነበረ። የቀድሞው የስዊድን ዋና ጳጳስም እህት አና ሃማር ግብረሰዶማዊና ከሌላ ሴት ጋር የምትኖር ካህን ነኝ ባይ የግብረሰዶማዊነትም አራማጅ ናት።

Other extreme examples in other countries:

- Case of USA

(there are documented information showing that the problem is/was in its heights in some States like ~~California~~. We have even worse stories in Massachusetts's. Info available at: http://www.protectmarriage.com or more particularly at http://www.protectmarriage.com/video . Visit also http://www.bpnews.net/BPnews.asp?ID=29197)

**የግብረሰዶማዊነት አራማጅነት በአገራችን ላይ በምን መልኩ እየተካሄደ ይገኛል?**

How is homosexual lobbying working in our Country Ethiopia at present?

**የግብረሰዶማዊነት አራማጅነት በአገራችን ላይ እየሰራ ስለሚገኝባቸው መንገዶች ጭብጥ መረጃዎች አሉን?**

1. በኢትዮጵያ ውስጥ ብዙ የእርዳታ ስራ የሚያካሂደው የስዊድን ዋነኛ የእርዳታ ድርጅት - ሲዳ - በግብረሰዶም ጉዳይ ላይ ያለውን የአራማጅነት ስራ እስቲ እንመልከት። በሲዳ ድረገጽ ላይ "SIDA's work on Lesbian, Gay, Bisexual and Transgender issues in international development cooperation" የሚባልን አንድ ዶክዩመንት ማግኘት ይቻላል። ይህ ዶክዩመንት ሲዳ አለም አቀፍ የእርዳታ ስራውን መሳሪያ በማድረግ በግብረሰዶማውያን፣ በባይሴክሹአልና ተራንስሴክሹአል ግለሰቦች ዙሪያ ምን ሊያደርግ እንደሚያስብ ገሃድ አድርጎ ያቀረበበት ዶክዩመንት ነው። ከይዘቱ በከፊል ከዚህ በታች ተርጉመን አስቀምጠናል።
    - <<ስዊድን አነጋጋሪ የሆኑ ጉዳዮችን ማንሳትና አነሳሽ እርምጃዎችን መውሰድዋን ትቀጥላለች። ተመሳሳይ አስተሳሰብ ካላቸው ቡድኖችና አገሮች ጋር በመስራት ቀስ በቀስ ውጤት ማግኘት እንደሚቻል ከልምዳችን እናውቃለን።>>
    - <<ከሌሎች ስታራተጂካል እንቅስቃሴዎቻችን በተዘማችነት ስዊድን ትኩረትዋን በሌዝቢያን፣ ጌይና ባይሴክሹአል እንዲሁም ትራንስሴክሹአል ግለሰቦች ላይ ታደርጋለች። ስዊድን በአለም አቀፍ ስራዋ ውስጥ ስለጾታ ግንዛቤና ስለወሲባዊ ዝንባሌ (ሴክሹአል ኦሪየንቴሽን) ጉዳይ ላይ ንቃት

እንዲኖርና እውቀት እንዲጨምር ለማድረግ ትጥራለች። እንዲሁም ግብረሰዶም የሆኑ፣ ባይሴክሹአል የሆኑና ጾታቸውን የቀየሩ ሰዎችን ማግለል የሰውን ልጅ መብት መጣስ በመሆኑ ትኩረት እንዲሰጠው ትጣጣራለች። ስዊድን በምትረዳቸው 70 አገሮች ውስጥ ግብረሰዶማዊነት ሕገወጥ ድርጊት ነው። ስዊድን እነዚህ ህጎች እንዲለወጡና ሕገወጥ መሆኑ እንዲቫርና ከላይ የተጠቀሱ ግለሰቦች መብታቸው እንዳይጣስ መከላከያ እንዲደረግላቸው ለማድረግ ትሳራለች።>>

- <<... የግብረሰዶማውያን ጉዳይ የመብት ጉዳይ እንደሆነና ከጾታ እኩልነት ጋር በአንድ አይን እንዲታይ መጣርና ያንንም መጣስ በሕብረተሰቡ ፍትህ እንደማጉደል እንዲቆጠር ለማድረግ ነው>> የሚል ይግኝበታል!!!
- ለመሆኑ ስዊድን እንዲህ መሰሉን ጣልቃ ገብነት በእርዳታ ስም እንድታካሂድ ፈቃድ የሰጣት ማን ነው? በሌላው አገር የሞራል ጥያቄዎች ውስጥ ጣልቃ በመግባት ሕግ እንዲቀየር ወ.ዘ.ተ. የማድረግ ጣልቃ ገብነት የባሕል ቅኝ ግዛት ካልሆነ ምን ስያሜ ሊሰጠው ይችላል? እንደዚህ አይነቱ ከበስተጀርባው ሌላ አጀንዳ ያለበት እርዳታስ ለኢትዮጵያ ምን ይፈይዳል ነው? ገንዘባቸውን ሰጥተውን ነፍሳችንን ከሚወስዱብን፣ ባሕልና ሃይማኖት አልባ አድርገው እርቃን ከሚያስቀሩን እርዳታቸው ጠሳችንን ለምን አይወስድም!!!
- <<እግዚአብሔር ሆይ፤ በእርዳታ ስም ከሚመጣ የባሕል ቅኝ አገዛዝና የሞራል አተላ ምድራችንን እባክህ ታደጋት>>

2. ስለወሲብ ለሕብረተሰብ መረጃ በመስጠት የታወቀውና ከግብረሰዶማዊነት አራማጅ ድርጅቶች ጋር በጣምራ የሚሰራው አረ. ኤፍ. ኤስ. ዩ. የተባለው የስዊድን ድርጅት ከኢትዮጵያና ከሌሎች የአፍሪካ አገሮች የወጣቶች መሪዎችንና አስተባባሪዎችን ወደስዊድን ስኮላርሺፕ ሰጥቶ በመጋበዝ፣ በኮርሱ ላይ ስለግብረሰዶም ጉዳይ ሃይለኛ <<ንቃትን>> በመስጠት ግብረሰዶማዊነትን በአገራችን ለማስፋፋት ተጨባጭ እርምጃ ወስዷል። በኮርሱ ላይ የተገኙት ኢትዮጵያውያን ለዚህ ሎቢ ባይከፈቱም ከሌሎች የአፍሪካ አገሮች የመጡት ልዑካን ግን ወደአገራቸው ሄደው ይሄንን ማለትም ግብረሰዶማዊነት ተቀባይነት እንዲኖረው ለመስራትና ለማስፋፋት ወስነው እንደሄዱ ታዝበዋል።
   - ይህም ጉዳይ እንደሲዳው ሁሉ በሌላ ደሃ አገር በእርዳታ ስም የሚደረግ ጣልቃ ገብነትና የግብረሰዶምን ክፉ አጀንዳ ከማራመድ ተለይቶ የማይታይ ጉዳይ ነው!!
3. Lobbying for a “gay march”???
4. United Nations taking up this abomination because of different countries lobbying for this!

<<ክብራቸው በነውራቸው ነው>>

# የግብረሰዶማዊነት አራማጆች / Homo-Lobbying

በዚህ ዘጋቢ ፊልም <<የግብረሰዶማዊነት አራማጆች>> ወይንም <<ሆሞ ሎቢ>> ብለን የምንጠራቸው ግብረሰዶማውያን አሉ። እነዚህ ሰዎች ግብረሰዶማዊነትን የእኩልነትና የመብት ጥያቄ በማድረግ ግብረሰዶማዊነትና ግብረሰዶማውያንም በሕብረተሰብ ተቀባይነት እንዲኖራቸውና የስልጣን ስፍራ አግኝተው ተቃዋሚዎችን

ጸጥ እንዲያሰኙ ከፍተኛ ጠርነት የሚያካሂዱ ግለሰቦች ናቸው። በአገራችን ይህ እንቅስቃሴ ምናልባት ገና በሙላት ስላልገባ ስፍራ አግኝቶ ስልጣን ሲይዝ ምን እንደሚመስል ማሰብ በጣም አዳጋች ሊሆን ይችላል። በምእራቡ ዓለም የምንኖር ኢትዮጵያውያን ግን በየቀኑ የሚገጥሙን እጅግ አሳዛኝና አስደንጋጭ ክንዋኔዎችን ስንገልጽ አንዳንዶቹ ለማመን የሚያስቸግሩ ሊመስሉ ይችላሉ። ከዚህ ቀጥሎ ባለው ገለጻ የግብረሰዶማዊነት አራማጆች በአሜሪካ በግልጽ በማይታይ ስዋራ አሰራር ግብረሰዶማዊነትን እንዴት ወደሕብረሰተሰብ አሹልከው እንደሚያስገቡና ምን ያህል ደረጃ እንደደረሱ እንመለከታለን።

## <<ግብረሰዶማዊነትን አሜሪካ እንድትቀበለው ማድረግ>> (Selling homosexuality to America)

- የግብረሰዶማዊነት አራማጆችን ስውር አጀንዳና አሰራር ማጋለጥ (Exposing the gay agenda)

  ፖል ኢ. ሮንዶ የሚባለው የስነ ንግድ ትምሕርት ምሩቅና ሞያተኛ ሆኖ የግብረሰዶማዊነት አራማጆች በስውርና በግልጽ ሆን ብለው ያቀዱትን፣ ተመካከረው የደረሱበትን ስምምነትና ውጥን ባደረገው ጥናትና ምርምር ሊዋሹ በማይችሉ ተጨባጭ ማስረጃዎች አጋልጦ ጽፎአል። ዝርዝር ሃተታውን በሚከተለው ድረ ገጽ ማግኘት ይቻላል http://www.lifeissues.net/writers/rond/shta/shta_01sellinghomosexuality1.html

  በዚህ ጽሑፍ ላይ ከተነሱት ሃሳቦች አንዳንዶቹን ከዚህ በታች አቅርበንላችኋል።

- ለሽያጭ የሚቀርበውን እቃ በአዲስ ሁኔታ አሽጎ ማቅረብ ትልቁና ዋነኛው የግብረሰዶማዊነት አራማጆች አጀንዳ ነው! ግብረሰዶማዊነትን የሞራል ጥያቄ እንዳልሆነ፣ ነገር ግን ማንም ምንም የማድረግና እንደፈለገው የመኖር መብቱ ሊጠበቅለት ይገባል በሚል ሰበብ ለዚህ ክፉ አኗኗር በመብት ሰበብ መከራከር ቀዳሚና ዋነኛ ስልታቸው ነው!!! (ቀደም ሲል <<የግል ሕይወቴ ነው፣ ሰው ምን አገባው?>> ወ.ዘ.ተ. ለሚሉት የመከራከሪያ ሃሳቦች ሁሉ ስለግብረሰዶ ሕይወት መዘዞችና ግለሰቡ እራሱን፣ ሕጻናትን፣ ቤተሰብንና ሕብረተሰብንም እንደሚጎዳ ተመልክተናልና በዚህ አጋጣሚ ብዙ መናገር አያሻንም)
- የግብረሰዶማዊነት አራማጆች የአሜሪካን መገናኛ ብዙሃን (ማስ ሚዲያ) በመቆጣጠር ሰው እስኪሰለቸውና ጆሮው እስኪደነዝዝ ድረስ ያለማቋረጥ ስለግብረሰዶማዊነት ማውራት (ጃሚንግ) የሚባል ዘዴን ይጠቀማሉ። እንዲሁም ከሆሊውድ ጋር አብሮ በመስራት ግብረሰዶሞችን እንደምስኪንና መብት እንደተነፈጉ አድርጎ በልብወለድ ፊልሞች በማቅረብ የሰው አይምሮ ግብረሰዶማዊነትን ፍጹም እስኪለምደውና ነውርነቱ እንኪወገድ የሕብረተሰብን ሕሊና በማደንዘዝ ዘመቻን ያካሂዳሉ!
- ግብረሰዶማውያን አራማጆች ሬቶሪክን (ወይንም በተደጋጋሚ የሚባልና ሰው ውስጥ የሚቀር አባባልን) በመጠቀም ጥበብ የተሞላው አባባልን በመጠቀም በንግግር መርታትንና ሃሳብን ተቀባይ በማድረግ ሕብረተሰብን የመማረክ ዘዴን ይጠቀማሉ።

- በታገሱን (ቶለራንስ) ቋንቋ በመጠቀም ስፍራ ማግኘት አንዱ ስልታቸው ነው። እነርሱ ግን ሌላውን ለመታገስ ቀርቶ የማይወዱት ነገር የተባለ እንደሆነ ሰውየውን ለማጥቃት አይመለሱም።
- ግብረሰዶማዊነት በትምሕርቱ አለም ላይ ተጽእኖ አድርጎ ግብረሰዶማዊነት እንደማንኛውም የኑሮ ዘይቤና በተፈጥሮ የሚመጣ ሆኖ እንዲታይ ማድረግ ሌላው አይነተኛ ስልታቸው ነው።
- ግብረሰዶማውያንን እንዲያውም ከሌሎች ይልቅ የሚደነቁና የኑሮ ዘይቤአቸው ሊሞከር የሚገባው እንደሆነ በመሳል ቅስቀሳ ያደርጋሉ።
- በምንም አይነት ሁኔታ ስለግብረሰዶም ክፉ ገጽታዎች እንዳይነሱ ማድረግ። ለምሳሌ፤ ኤድስ፣ ራስን ማጥፋት፣ ካንሰር፣ ዲፕሬሽን ወ.ዘ.ተ.) የግብረሰዶማዊ ኑሮ መዘዞች ሲሆኑ እነዚህ እንዳይሰሙ (ትኩረት እንዳይሰጣቸው) የሚቻለውን ያደርጋሉ።
- የግብረሰዶማዊነት ኑሮ በጥቅሉ በሰዎች ተቀባይነት እስኪያገኝ ድረስ ከግብረሰዶማዊነት ጋር አብረው የሚመጡ እጅግ ዘግናኝ ነገሮችን ፈጽሞ አለማንሳት እንዳለባቸውም ጠንቅቀው ያውቃሉ።
- ስለግብረሰዶማዊነ ተግባራት ፍጹም አለማውራት አለመግለጽ። (እጅግ ነውርና ዘግናኝ ጸያፍም ስለሆኑና ግብረሰዶማውያን ስለሚለማመዷቸው ልምምዶች መጀመሪያ ላይ ምንም አያነሱም። አንዴ ግብረሰዶማዊነትን ሕብረተሰብ ከተቀበለላቸው በኋላ ግን ቀስ በቀስ አንዳንድ በምእራቡ አለም የሚታዩ የግብረሰዶማዊነት አራማጅ ድርጅቶች እንደሚያደርጉት አፍቃር ሕጻንነትን ወይንም ፒዶፊሊን እንኳን ሕብረተሰብ እንዲቀበለው ለማድረግ ሲጥሩ ይገኛሉ።
- ሳይንሳዊ ጥናትን በመጠምዘዝ (ማኒፑሌት በማድረግ) ሊደገሙ ያልተቻሉ ሃሰተኛ የጥናት ውጤቶች በማቅረብ <<እንዲህ ሆኜ ነው የተወለድኩት>> <<ማንነቴን ልቀይረው አልችለም>> የሚሉ መላ ምቶች በማቅረብ ሃዘኔታና ተቀባይነትን ከሕብረተሰብ መሻት
- ግብረሰዶማዊነማዊነት <<የሞራላዊ ምርጫችሁ ውጤት ነው>> ተብለን እንባላለን በማለት <<በምርጫ የሚመጣ ነው>> የሚለውን ሃሳብ ፈጽሞ ይቃወማሉ ያጠቃሉም።
- አንዳንድ ቀዝቀዝ ያሉ ቤተክርስቲያኖችንም በመርታት ግብረሰዶማዊነትን እንዲቀበሉ ማድረግና በእነርሱ ሕብረተሰብን ውስጥ ተቀባይ መሆንን መጣር ሆን ብለው የሚከታተሉት ስልት ነው!
- ግብረሰዶምን የሚቃወሙ ግለሰቦችን ተከላካይ (ዲፊንሲቭ) እንዲሆኑ ማድረግና ማጥቃት ዋነኛ ስልታቸው ነው!! የግብረሰዶማዊነት የኑሮ ዘይቤ ላይ ጥያቄ ያላቸውና መልካም እንዳልሆነ ሊናገሩ የሚደፍሩ ሲኖሩ አራማጆቹ እነዚህ ከሚከሱበትና ከሚያጠቁባቸው ዘዴዎች መካከል፤
    - o የግብረሰዶማውያን ፍርሃት/ጥላቻ ያላቸው (ሆሞፎብ) ሆነው እንዲቆጠሩ ማድረግ
    - o እነዚያ ግለሰቦች የእራሳቸውን ግብረሰዶማዊ ፍላጎት ለመሸፈን እንደሚቃወሙ በመናገር ተከላካይ (ዲፌንሲቭ) ማድረግና ማጥቃት!
    - o በሌሎች ላይ አለአግባብ የሚፈርድ ራስን አመጻዳቂ ሰው (ቢጎት) ነው ብሎ መክሰስ
    - o ናዚዎች ግብረሰዶማዊነትን ተቃውመዋልና እናንተም ከእነርሱ የማትሻሉ ናችሁ ብለው የሌለ ጥቃት ያቀርባሉ። የዚህ የኑሮ ዘይቤ

ተቃዋሚዎች ከዚያ ለላመፈረጅ ሲሉ የግብረሰዶም መብት ተከራካሪዎች ደጋፊ እንዲሆኑ የስነልቡናዊ ጫና ይፈጥሩባቸዋል።

- ለግብረሰዶማውያን የጸረ-ግለላ (አንቲ-ዲስክሪሚኔሽን) ሕግ እንዲወጣ ማድረግ
- የጥላቻ ማነሳሳት (ሄት ስፒች) የሚባለው ሕግ ላይ ግብረሰዶማዊነትም እንዲገባና ግብረሰዶማዊነትን ተቃውሞ የሚነገር ነገርን ሁሉ (በቤተክርስቲያን ሳይቀር) በሆነ የሕብረተሰብ ክፍል ላይ ጥላቻን እንደሚዘራ አድርጎ ማቅረብ ትልቅ ስትራተጂያቸው ነው።

<<አምላክ ሆይ፤ በግብረሰዶማዊነት ከመወረስ ኢትዮጵያን ጠብቃት!!!>>
(ትእይንት 8 መጨረሻ)

**እንዴት ወደሕብረተሰብ ውስጥ እራሳቸውን እንደሚያስገቡ፤**

The different levels of insertion into society

(I would recommend that the discussion under this title may be kept minimum)

1) መጀመሪያ ግብረሰዶማዊነት ወንጀል በሆነባቸው አገሮች ወንጀል መሆኑ እንዲሻር ያላሰለሰ ጥረት ያደርጋሉ·Getting homosexuality “decriminalized”
2) Getting homosexuality “declassified” from being a sickness to a “disorder” and then an inclination (orientation)
3) Changing the psychiatric association to change it's decree about homosexuality
4) Getting Partnership laws constituted
5) Getting the apostate Church to accept homosexuality and take away the stigma of being a homosexual by letting well known figures appear in the media and admit they are gay!
6) Lobbying in society on the issue of “rights” and diverting the issue of morality into an issue of human rights!
7) Getting homosexuality to be accepted as an alternative lifestyle
8) Getting in the rest of the “gear” – more extreme practices – even acceptance of paedophilia etc!
9) God only knows where this will end… .

## ታዲያ ምን እናድርግ?

ግብረሰዶማዊነት ሲስፋፋና የግብረሰዶማዊነት አራማጆች አጀንዳ በሕብረተሰብ ብቅ ብቅ ማለቱን ስንመለከት በግለሰብ፣ በቤተሰብ፣ ቤተክርስቲያን ወይንም በሃይማኖት ድርጅቶች ደረጃና በሕብረተሰብም ደረጃ ልናደርግ የምንችለው ምን ምን ይሆን? ይሄንንስ በተመለከተ ዛሬ በግብረሰዶማዊነት አራማጆች ክፉ አጀንዳ ከተወረሰው ከምእራቡ አለም ልንማር የምንችለው ትምሕርት አለን?

### ሀ) በግለሰብ ደረጃ ምን ማድረግ እንችላለን?

የግብረሰዶማዊነት አራማጆች በመብት ሰበብ በጣም አድርጎ የሌሎችን የንግግርና ሃሳብን የመግለጽ እንዲሁም የሃይማኖት ነጻነትን የሚጋፋና የሚዋጋ አካሄድ ቢኖራቸውም ምንም ሳንፈራ ለምናምነው እውነት መቆም ይገባናል። ግብረሰዶማዊነት ጸያፍ ኃጢአት መሆኑን መጽሐፍ ቅዱስ እንደሚያጸና በመግለጥ ለምናምነው ነገር ያለፍርሃት መቆም ይኖርብናል።

<<*ሥጋንም የሚገድሉትን ነፍስን ግን መግደል የማይቻላቸውን አትፍሩ*>> (ማቴ 10፥28)

**የግብረሰዶማዊነት መንፈስን መስፋፋት**

What can/should we do as an individual?

- የምልጃ አገልግሎት (ሃይለኛውን ማሰር)
- ሳይፈሩ ለእውነት መቆም
- ልጆች ወደጸታ ግንዛቤ መዛባት እንዳይገቡ መከላከል
- በጌታ Be bold!
- "Fear not those who can only kill the body" - Be prepared to pay the ultimate sacrifice
- Protect our Children from falling into gender identity disorder by being a raw model and building a good and loving relationship during the child's upbringing.
- Can one come out of homosexual lifestyle and desire? **አዎን ይቻላል**! (We may refer to the research by Dr. *Charles Socarides, Lecturer Stanton Jones, Ph.D. entitled* "Can Homosexuals Change? Is the Attempt Harmful?". Visit: http://www.narth.com/videos/video9.html)

## ለ) በቤተሰብ ደረጃ ምን ማድረግ እንችላለን?

1. ከሁሉ አስቀድመን ለልጆቻችን መጸለይና በእግዚአብሔር ፍርሃት እንዲያድጉ መጽሐፍ ቅዱስን እያስተማርናቸው ማሳደግ ትልቁ የወላጅነት ሃላፊነታችን ነው።
2. አባቶች ለልጆቻቸው ጊዜ በመስጠት ተባታዊ የጾታ ግንዛቤን በወንድ ልጆቻቸው ውስጥ ማጎልበት ይኖርባቸዋል! (አልዓዛር ገዳሙ)
3. ወንዶች ልጆች ከእናታቸው ጋር ያላቸውን መያያዝ ቀነስ አድርገው ከአባታቸው ጋር በሚኖራቸው ጊዜ ማሳለፍ ተባታዊ የጾታ ግንዛቤን (ማስክዩሊኒቲን) በማሳደግ የወንድነትን ባሕርይ እንዲያፈሩ ያስፈልጋል! (መሰረት ዓለሙ)
4. በአጠቃላይ ፍቅር የሞላበት መልካም ግንኙነት ከአባት ጋር መጎልበት ግብረሰዶማዊነት የመከላከያ አይነተኛ መሳሪያ ነው!
5. ወንዶች ልጆች በልጅነታቸው ከአባቶቻቸው ጋር አከላታቸውን እንዲታጠቡ መፍቀድና <<እኔና አባቴ አንድ አይነት ነን>> የሚል ስሜት እንዲያድርባቸው ማድረግ
6. በአጠቃላይ እናት በጉርምስና እድሜ ላይ ወደኋላ ብላ አባት በማደግ ላይ ያለውን ታዳጊ ወጣት አዋቂ ወንድ ወደመሆን እድገት እንዲያመጣው ወንድ ልጇን ለባልዋ ለቀቅ ልታደርግ ይገባል! (ጽዮን ወሰኑ)
7. በአጠቃላይ ፍቅር የሞላበት መልካም ግንኙነት ከአባት ጋር መጎልበት ግብረሰዶማዊነት የመከላከያ አይነተኛ መሳሪያ ነው!

8. እራሳቸው የጾታ ግንዛቤ ችግር ሊኖራቸው ስለሚችል ታናናሽ ወንዶች ልጆችን ጉርምስና እድሜ ካሉ ወንዶች ጋር ብዙ ጊዜ እንዲያሳልፉ ዝም ብሎ መተው አይገባም እስኪሉ ድረስ ይላሉ ባልሙያዎቹ
9. በተጨማሪም <<ታሞ ከመማቀቅ አስቀድሞ መጠንቀቅ>> እንዲሉ ልጆቻችን የጾታ ግንዛቤ መዛባት ውስጥ እንዳይወድቁ እያበረታታናቸው ክፉን ተጽእኖ ለመከላከል የሚያስችል መልካም ግንኙነትን ከእነርሱ ጋር ማጎልበት አይነተኛ ነገር ነው።

## ሐ) በቤተክርስቲያን ደረጃ ምን ልናደርግ እንችላለን?

የገሃነም ደጆች አይችሉአትም የተባለላት ቤተክርስቲያን የእግዚአብሔርን ፈቃድ እውቀት ተሞልታ እግዚአብሔር ባስቀመጣት ስፍራ ስትመላለስና ስታበራ በምድር ላይ ታላቅ የእግዚአብሔር ዓላማ መገለጫ ናት። ስለዚህም ግምባር ቀደም ተልእኮዋ የሆነውን ሙሉውን ወንጌል የመስበክ አገልግሎቷን በሙላት መወጣቷ አይነተኛ ሃላፊነትና ድርሻዋ ነው። እግዚአብሔር በምድር ላይ ላለችው የክርስቶስ አካል ከሰጣት ዋነኛ ስልጣን መካከል የክፉውን ሃይል በምድር የማሰር አገልግሎት ነው። በምልጃ አገልግሎቷም በክርስቶስ ኢየሱስ ስም የሰይጣንን አሰራር ሁሉ ማፍረስና አላማውን ማኮላሸት ትችላለች። በእግዚአብሔር ፈቃድ የታሪክን ሂደት በጸሎት መቀየስም አይነተኛ የቤተክርስቲያን የምልጃ አገልግሎት ነው። ቤተክርስቲያን በምድር ላይ ብርሃንና ጨው ከምትሆንባቸው መንገዶች አንዱና ዋነኛው የእግዚአብሔርን እውነት በግብረሰዶማዊነት ጉዳይ ቁልጭ አድርጋ በማስተማር የአራማጆችን ውሸት በእግዚአብሔር እውነት ማራቆት ትችላለች። የእውነት አምድ የሆነችው ቤተክርስቲያን ለማያምነው አለም እንኳን ታላቅ የሕሊና ደወልና የእግዚአብሔር የትንቢት ድምጽ ናት!

<<በእናንተ ስላለ ተስፋ ምክንያትን ለሚጠይቁዋችሁ ሁሉ መልስ ለመስጠት ዘወትር የተዘጋጃችሁ ሁኑ፥ ነገር ግን በየዋህነትና በፍርሃት ይሁን።>> (1ኛ ጴጥ. 3፡15)

ቤተክርስቲያን ሳታመቻምችና ሳትፈራ፣ ግብረሰዶማዊነት ኃጢአትና ርኩሰት መሆኑንና የእግዚአብሔርን ፍርድ በአገር ደረጃ የሚያመጣ ነገር መሆኑን ማስተማር ይገባታል። እንዲሁም የእግዚአብሔር ቤተክርስቲያን ላለችበት ሕብረተሰብ ብዙ ሃላፊነት ያለባት መሆኑን ተገንዝባ ግዴታዋን በሁሉ ረገድ መወጣት ይገባታል ብለን እናምናለን።

አንዳንዶች <<ቤተክርስቲያን ወንጌልን መስበክ ነው የሚገባት እንጂ እንደዚህ አይነቱ ማሕበራዊ ነገር ውስጥ መግባት ምን ያስፈልጋታል?>> የሚል ሃሳብ የሚኖራቸው ይኖራሉ።

በመሰረቱ የክርስቶስ ኢየሱስ ወንጌል የሰውን ሁለንተና (ማለትም መንፈሳዊ፣ ስነልቡናዊና ቁሳዊ ጥያቄዎች) በተመለከተ መልእክት ያለው ነው። ለምሳሌ ያህል፤ ኤች. አይ. ቪ. ኤድስን በተመለከተ በሕብረተሰብ ውስጥ ያለውን ችግር ስናነሳ መታቀብን መስበክ የምትችለው በዋነኝነት ቤተክርስቲያን ናት። ጽንስ ማስወረድን በተመለከተ የሰው ልጅ ሕይወት የሚጀምረው ገና በተጸነሰ ጊዜ መሆኑን ከቃሉ ግልጽ አድርጋ ማስረዳት የምትችል ቤተክርስቲያን ናት። ስለዚህ ማሕበረሰባዊ በሆኑ ጉዳዮች ቤተክርስቲያን ይህ ነው የማይባል ሚና ሲኖራት ሕብረተሰብ የሚወስደውንም አቅጣጫ እንደእግዚአብሔር መንግስት ሃሳብ ልትቀርጽ ይገባታል።

በዚህም ዘመን እንደዳንኤል፣ እንደነሕምያ፣ እንደዳዊትና እንደሌሎቹም ጌታ አላማውን እንደፈጸመባቸው ሰዎች እንዲጠቀምብን ከክልላችን ወጥተን ለአካባቢያችንና ለአገራችን ሃላፊነት መውሰድን ልንለማመድ ይገባናል።

<<ከእነርሱ ግን የቆጵሮስና የቀሬና ሰዎች የነበሩት አንዳንዶቹ ወደ አንጾኪያ መጥተው የጌታን የኢየሱስን ወንጌል እየሰበኩ ለግሪክ ሰዎች ተናገሩ።የጌታም እጅ ከእነርሱ ጋር ነበረ፤ ቍጥራቸውም እጅግ የሚሆን ሰዎች አምነው ወደ ጌታ ዘወር አሉ።

ሐዋ 11፤20-21

## በአገርና በሕብረተሰብ ደረጃ ምን እናድርግ?

- ስለግብረሰዶምነት ጉዳይ አራማጆች በሚነዙት የተሳሳተ ትምሕርትና ለክፉ አሰራራቸው ልባችንን አለመክፈት
- ልጆቻችንን ከክፉ ጥቃት የሚጠብቁ ሕግጋትን መደንገግ።
- ግብረሰዶማዊነት ጎጂ እንደሆነ ታውቆ በሕብረተሰብ ውስጥ ሊኮነንና ነውርነቱ እንደተጠበቀ ሊቆይ ያስፈልጋል። ይህ ሲሆን ብቻ ግብረሰዶማዊነትን የሚለማመዱ ግለሰቦች ከዚህ ጎጂ ልምምድ ለመውጣት ጥረትን ያደርጋሉ። በአንዳንድ ምእራባውያን አገሮች የአራማጆችን ሃሰት ተቀብለው የግብረሰዶምነትን ነውርነት ለመሻር ብዙ ተጥሯል። ታዲያ በእነዚህ አገሮች ግብረሰዶማውያን ይሄንን የኑሮ ዘይቤ እንዲቀይሩ ማበረታታት እንደስህተት ስለሚቆጠር ግብረሰዶማውያን ከዚህ ኑሮ የመውጣት እድላቸው እየመነመነ፣ ወደዚህ ሕይወት የሚገቡ ታዳጊ ወጣቶች ቁጥር እየጨመረ መጥቷል። ይህም አሳዛኝ ነገር ነው።
- የውጪ ድርጅቶችና መንግስታት እርዳታን ተገን አድርገው ለሚያቀርቡት ግብረሰዶማዊነትን በተመለከተ የኢትዮጵያ ሕግ እንዲለወጥ ወ.ዘ.ተ. የሚያቀርቡትን ቅድመ ሁኔታ ፍጹም በአገራችን የግብረገብነት ኑሮ ጣላቃ ገብነት ስለሆነ ለዚህ አይነቱ የባሕል ቅኝ አገዛዝ እጅ አለመስጠት!
- አገራችን ኢትዮጵያ ከምእራቡ አለም ስትስተያይ ዛሬ ያላትን ይሄንን የግብረገብ የበላይነት ጠብቃ እንድትኖር ማድረግና የምእራባውያንን ባእድና ጎጂ ባሕል አለመቅሰም።
- We (those of us living abroad) want to come to live in our native country as we hope this will be the sanctuary (the safe haven) to escape our Children from being infiltrated with this disgusting abomination!

መልካም መሳሌዎች፤
- መጋቢ ኦከ ግሪን

Good commendable examples (raw-models):

- Pastor Åke Green
- Ron Lindén
- Great men of faith and bold preachers are good examples in the US!

# እዚህ ኑሮ ውስጥ የገባ ሰው እንዴት መውጣት ይችላል?

# ግብረ-ሰዶምንና ግብረ-ሰዶማዊነትን መለየት

- ጥላቻ አይገባም
- በተለያዩ አስገዳጅ ሁኔታዎች ወደዚህ ህይወት ለገቡ መራራት
- ከዚህ ህይወት ለመውጣት እንዲችሉ መርዳት

አይን ያፈጠጠ ክፉ ኑፋቄ ላይ ያለን ካልሆነ በስተቀር በግብረሰዶማዊነት ሕይወት ስለመኖር ቅዱሳት መጻሕፍት የሚሉት ግልጽና የማያወላዳ ነገር ነው። ግብረሰዶማውያን የእግዚአብሔር ቃል በሚለው ደረጃ በሃጢያት ኑሮ ውስጥ እንዳሉ ሰዎች ተደርገው መታየት ይኖርባቸዋል። ሃጢያት ደግሞ በባሕሪይ ደረጃ ሊለመድ እንደሚችልና በዚህ ደረጃ ለተጠመደው ሰው ከዚህ ልምምድ መውጣት የማይወጣ ዳገት ሊሆን እንደሚችልበት ሊታወቅ ይገባል። ሃጢያትን በሚጠላ ሃጢያተኞችን ግን በሚወድ አምላክ የምናምን ሰዎች ግብረሰዶማዊውን ሰው ከጸያፉ የግብረሰዶማዊ ባሕሪይ ለይቶ ማየት አስፈላጊ ይሆናል።

በዚህ ዝግጅት ለማየት እንደሞከርነውም ግብረሰዶማዊነት ጸያፍ ሕይወትና በዚህ ሕይወት የሚመላለሱትንም ሆነ ሎሎችንም የሕብረተሰብ ክፍሎችን እጅግ የሚጎዳ የኑሮ ዘይቤ እንደሆነ ተመልክተናል። ሆኖም በተለያየ ምክንያት በዚህ ወጥመድ ውስጥ ገብተው ለመውጣት እየፈለጉ አቅቷቸው ለሚቸገሩ ሰዎች የሚገባውን ፍቅርና ርሕራሄ ማሳየት ይልቁንም ከመንፈሳውያን ሰዎች የሚጠበቅ ጉዳይ ነው። በተለይ ደግሞ ገና በለጋ እድሜ ላይ ሳሉ በሌሎች ማባበል ወይንም አስገዳጅነት ወይንም በተበላሸ የቤተሰብ ግንኙነት ምክንያት ለዚህ ክፉ ሕይወት ሰለባ ለሆኑት ርህራሄ ማሳየትና የእርዳታ እጅንም መዘርጋት ተገቢ ነው። ስለዚህ የኑሮ ዘይቤውን ብንጠላና ክፉ እንደሆነ ብንናገርም ግለሰቦቹን ግን ከሃጢአቱ ለይተን ማየት ይኖርብናል። እግዚአብሔር ኃጢአትን እንደሚጠላ ኃጢአተኛውን ግን እንደሚወድ አጥብቀን ልናውቅ ይገባናል።

ሌላው ልንረዳ የሚያስፈልገን ነገር ደግሞ ግብረሰዶማውያን የሆኑቱን ግለሰቦች ከግብረሰዶማዊት አራማጆች ለይተን ማየት ይኖርብናል። በአራማጅነት የቆመ ሰው ሆን ብሎ ለዚህ ርኩሰት ተቀባይነትን የሚሻ ሲሆን ሌሎች ግን አራማጆቹ የሚነዙትን ውሸት ያልተቀበሉ ነገር ግን በግብረሰዶማዊ ፍላጎታቸው የሚቸገሩ፣ የሚያፍሩና <<ማን ባላቀቀኝ?>>፣ <<ችግሬን ማን በተረዳልኝ?>> እያሉ በውስጣቸው የሚያለቅሱ ስለሚኖሩ እነዚህን ከአራማጆች ጋር መፈረጅ ስህተት ይሆናል።

ይሄንን ዘጋቢ ፊልም ለምትመለከቱና በግብረሰዶማዊነት ሕይወት እራሳችሁን ለምታገኙ ግለሰቦች ታላቅ የምስራች አለን። የምስራቹም <<ከዚህ ሕይወት መውጣት ይቻላል>> የሚል ነው!!! የኃጢአትን ቀንበር የሚሰብርና ከእስራትም የሚያወጣ የእግዚአብሔር ጸጋ አለላችሁ!!! እግዚአብሔር ከማንኛውም ሱስና እስራት እንደሚያላቅቅ ከግብረሰዶማዊነትም ያላቅቃል፣ ይፈታል ያወጣልም - ክብር ለእግዚአብሔር ይሁን!!

**ስለዚህ በዚህ ሕይወት ያላችሁና እርዳታ የምትፈልጉ ሰዎች ሁሉ አብረዋችሁ ሊጸልዩና በምክርና በክትትል ሊረዱአችሁ ዝግጁ የሆኑ ብዙ የእግዚአብሔር አገልጋዮች ስላሉ አይዞአችሁ! ይህን መሰል አገልግሎት በኢትዮጵያ ውስጥ ከሚሰጡ ተቋሞችና አገልግሎቶች አንዱ <<ዩናይትድ ፎር ላይፍ ኢትዮጵያ>> ተብሎ የሚጠራው አገልግሎት ነው። ቀድሞ ግብረሰዶማውያን የነበሩና በዚህ ሕይወት መመላለስ ምን ማለት እንደሆነ በራሳቸው ሕይወት ጠንቅቀው የሚያውቁ ብዙ ሰዎች ከዚህ የኑሮ ዘይቤ በእግዚአብሔር ቃልና በመንፈስ ቅዱስ ኃይል ተላቀው የሚኖሩ የእግዚአብሔር ምስክሮች አሉ። መጽሐፍ ቅዱስን ስለዚህ ይመሰክርልናል፤**

**<<...ወይስ ዓመፀኞች የእግዚአብሔርን መንግሥት እንዳይወርሱ አታውቁምን? አትሳቱ፤ ሴሰኞች ቢሆን ወይም ጣዖትን የሚያመልኩ ወይም አመንዝሮች ወይም ቀላጮች ወይም ከወንድ ጋር ዝሙት የሚሠሩ ... የእግዚአብሔርን መንግሥት አይወርሱም። <u>ከእናንተም አንዳንዶቹ እንደ እነዚህ ነበራችሁ፤</u> ነገር ግን በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም በአምላካችንም መንፈስ ታጥባችኋል፥ ተቀድሳችኋል፥ ጸድቃችኋል።>>** 1ኛ ቆሮ 6፣9-12.

**ዛሬም ቢሆን በጌታ በኢየሱስ ስምና በአምላካችንም መንፈስ ሰዎች ከግብረሰዶማዊነት ይታጠባሉ፣ ይቀደሳሉ፣ ይጸድቃሉም!!!**

Homosexuality must be accepted for what God says it is-- sin. Some homosexuals will attempt to circumvent the plain teaching of the Bible with the insipid reply that they are the way God made them. There is not the slightest bit of evidence in Scripture to support this false concept. God never created man with a so-called "homosexual need." No baby is born a homosexual. Every baby is born male or female. In every place the Bible refers to homosexuality, the emphasis is upon the perversion of sexuality. The practicing homosexual is guilty of "leaving the natural use of the woman" (<u>Romans 1:27</u>), meaning that his behaviour is "against nature" as in the case of the lesbian (<u>Romans 1:26</u>). Inasmuch as homosexuality is opposed to the regular law and order of nature, the genetic concept must be ruled out completely. If homosexuality were a genetic problem, there would be little hope for the homosexual simply because there is no way that the genes in a person can be changed.

- <<እግዚአብሔር ሃጢአተኞችን ይወዳል ሃጢአትን ግን ይጠላል>>
- የልጁም የኢየሱስ ክርስቶስ ደም ከኃጢአት ሁሉ ያነጻናል
- የእግዚአብሄር ጸጋ ህይወትን ይለውጣል
- 

Yes. <u>Romans 1:24-27</u>; <u>I Timothy 1:10</u> and <u>Jude 7</u>. If one takes these Scriptures seriously, homosexuality will be recognized as an evil. The Romans passage is unmistakably clear. Paul attributes the moral depravity of men and women to their rejection of "the truth of God" (1:25). They refused "to retain God in their knowledge" (1:28), thereby dethroning God and deifying themselves. The Old Testament had clearly condemned homosexuality but in

Paul's day there were those persons who rejected its teaching. Because of their rejection of God's commands He punished their sin by delivering them over to it.

- We are impressed by Jesus' compassion as He dealt with the outcasts of His society (the lepers). AIDS victims are the new lepers of the 21st century and Christians should be in the forefront of the battle to minister to these people – whatever reason for their illness.

We must always keep before us the fact that homosexuals, like all of us sinners, are the objects of God's love. The Bible says, "But God commendeth His love toward us, in that while we were yet sinners, Christ died for us" (Romans 5:8). Jesus Christ "is the propitiation for our sins: and not for ours only, but also for the sins of the whole world" (I John 2:2). The Christian who shares God's love for lost sinners will seek to reach the homosexual with the gospel of Christ, which "is the power of God unto salvation, to every one that believeth" (Romans 1:16). As a Christian I should hate all sin but I can find no justification for hating the sinner. The homosexual is a precious soul for whom Christ died. We Christians can show him the best way of life by pointing him to Christ. Our Lord said, "Go ye into all the world, and preach the gospel to every creature" (Mark 16:15). We are obligated to take the gospel to all.
http://www.bible.org/page.php?page_id=1302

# መጽሐፍ ቅዱስ ምን ይላል?

<<ከሴትም ጋር እንደምትተኛ ከወንድ ጋር አትተኛ፤ ጸያፍ ነገር ነውና።>>
ዘሌ 18:22

<<ኢሳይያስም እንደዚሁ፤ ጌታ ፀባዖት ዘር ባላስቀረልን እንደ ሰዶም በሆንን ገሞራንም በመሰልን ነበር ብሎ አስቀድሞ ተናገረ።>> ሮሜ 9፣29

<<ኃጢአትንም ያደርጉ ዘንድ ላሉት ምሳሌ አድርጎ ከተማዎችን ሰዶምንና ገሞራን አመድ እስኪሆኑ ድረስ አቃጥሎና ገልብጦ ከፈረደባቸው÷… >> (2ኛ ጴጥ 2፣6)

<<ማናቸውም ሰው ከሴት ጋር እንደሚተኛ ከወንድ ጋር ቢተኛ ሁለቱ ጸያፍ ነገር አድርገዋል ፈጽመው ይገደሉ ደማቸው በላያቸው ነው።>> ኦሪት ዘሌዋውያን 20፣13
<<እንዲሁም እንደ እነርሱ ዝሙትን ያደረጉና ሌላን ሥጋ የተከተሉ ሰዶምና ገሞራ በዙሪያቸውም የነበሩ ከተማዎች በዘላለም እሳት እየተቀጡ ምሳሌ ሆነዋል።>> የይሁዳ መልእክት 1፣7

<<የሰዶም ሰዎች ግን ክፉዎችና በእግዚአብሔር ፊት እጅግ ኃጢአተኞች ነበሩ።>> ኦሪት ዘፍጥረት 13፣13

<<እግዚአብሔርም በሰዶምና በገሞራ ላይ ከእግዚአብሔር ዘንድ ከሰማይ እሳትና ዲን አዘነበ>> ኦሪት ዘፍጥረት 19፥24

<<እግዚአብሔር በቍጣውና በመዓቱ እንደ ገለባበጣቸው እንደ ሰዶምና ገሞራ እንደ አዳማና እንደ ሲባዮ እንደ ሆነች ባዩ ጊዜ፥… >> ኦሪት ዘዳግም 19፥23

<<የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር ዘርን ባያስቀርልን ኖሮ፥ እንደ ሰዶም በሆንነ እንደ ገሞራም በመሰልነ ነበር።>> ትንቢተ ኢሳይያስ 1፥9

**<<እውነትን በዓመፃ በሚከለክሉ ሰዎች** በኃጢአተኝነታቸውና በዓመፃቸው ሁሉ ላይ የእግዚአብሔር ቍጣ ከሰማይ ይገለጣልና፤ እግዚአብሔር ስለ ገለጠላቸው፥ ስለ እግዚአብሔር ሊታወቅ የሚቻለው በእነርሱ ዘንድ ግልጥ ነውና። የማይታየው ባሕርይ እርሱም የዘላለም ኃይሉ ደግሞም አምላክነቱ ከዓለም ፍጥረት ጀምሮ ከተሠሩት ታውቆ ግልጥ ሆኖ ይታያልና፤ ስለዚህም **እግዚአብሔርን እያወቁ እንደ እግዚአብሔርነቱ መጠን ስላላከበሩትና ስላላመሰገኑት** የሚያመካኙት አጡ፤ ነገር ግን በአሳባቸው ከንቱ ሆኑ የማያስተውለውም ልባቸው ጨለመ። **ጥበበኞች ነን ሲሉ ደንቆሮ ሆኑ፥** የማይጠፋውንም የእግዚአብሔር ክብር በሚጠፋ ሰውና በወፎች አራት እግር ባላቸውም በሚንቀሳቀሱትም መልክ መስለው ለወጡ። **ስለዚህ እርስ በርሳቸው ሥጋቸውን ሊያዋርዱ እግዚአብሔር በልባቸው ፍትወት ወደ ርኵስነት አሳልፎ ሰጣቸው፤ ይህም የእግዚአብሔርን እውነት በውሸት ስለ ለወጡ በፈጣሪም ፈንታ የተፈጠረውን ስላመለኩና ስላገለገሉ ነው፤ እርሱም ለዘላለም የተባረከ ነው፤ አሜን። ስለዚህ እግዚአብሔር ለሚያስነውር ምኞት አሳልፎ ሰጣቸው፤ ሴቶቻቸውም ለባሕርያቸው የሚገባውን ሥራ ለባሕርያቸው በማይገባው ለወጡ፤ እንዲሁም ወንዶች ደግሞ ለባሕርያቸው የሚገባውን ሴቶችን መገናኘት ትተው እርስ በርሳቸው በፍትወታቸው ተቃጠሉ፤ ወንዶችም በወንዶች ነውር አድርገው በስሕተታቸው የሚገባውን ብድራት በራሳቸው ተቀበሉ። እግዚአብሔርን ለማወቅ ባልወደዱት መጠን እግዚአብሔር የማይገባውን ያደርጉ ዘንድ ለማይረባ አእምሮ አሳልፎ ሰጣቸው፤** ዓመፃ ሁሉ፥ ግፍ፥ መመኘት፥ ክፋት ሞላባቸው፤ ቅናትን፥ ነፍስ መግደልን፥ ክርክርን፥ ተንኰልን፥ ክፉ ጠባይን ተሞሉ፤ የሚያሾከሽኩ፥ ሐሜተኞች፥ አምላክን የሚጠሉ፥ የሚያንገላቱ፥ ትዕቢተኞች፥ ትምክህተኞች፥ ክፋትን የሚፈላለጉ፥ ለወላጆቻቸው የማይታዘዙ፥ የማያስተውሉ፥ ውል የሚያፈርሱ፥ ፍቅር የሌላቸው፥ ምሕረት ያጡ ናቸው፤ እንደነዚህ ለሚያደርጉት ሞት ይገባቸዋል የሚለውን የእግዚአብሔርን ሕግ እያወቁ እነዚህን ከሚያደርጉ ጋር ይስማማሉ እንጂ አድራጊዎች ብቻ አይደሉም።>> ሮሜ 1፥18-32

<<ወይስ ዓመፀኞች የእግዚአብሔርን መንግሥት እንዳይወርሱ አታውቁምን? አትሳቱ፤ ሴሰኞች ቢሆን ወይም ጣዖትን የሚያመልኩ ወይም አመንዝሮች ወይም ቀላጮች ወይም ከወንድ ጋር ዝሙት የሚሠሩ ወይም ሌቦች ወይም ገንዘብን የሚመኙ ወይም ሰካሮች ወይም ተሳዳቢዎች ወይም ነጣቂዎች የእግዚአብሔርን መንግሥት አይወርሱም። ከእናንተም አንዳንዶቹ እንደ እነዚህ ነበራችሁ፤ ነገር ግን በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም በአምላካችንም መንፈስ ታጥባችኋል፥ ተቀድሳችኋል፥ ጸድቃችኋል። ሁሉ ተፈቅዶልኛል፥ ሁሉ ግን አይጠቅምም። ሁሉ ተፈቅዶልኛል፥ በእኔ ላይ ግን አንድ ነገር እንኳ አይሠለጥንብኝም።>> 1ኛ ቆሮ 6፥9-12.

# መደምደሚያ

“ለቅዱሳን እንደሚገባ ግን ዝሙትና ርኵሰት ሁሉ ወይም መመኘት በእናንተ ዘንድ ከቶ አይሰማ፤ የሚያሳፍር ነገርም የስንፍና ንግግርም ወይም ዋዛ የማይገቡ ናቸውና አይሁኑ፥ ይልቁን ምስጋና እንጂ። **ይህን እወቁ፤ አመንዝራም ቢሆን ወይም ርኵስ ወይም የሚመኝ እርሱም ጣዖትን የሚያመልክ በክርስቶስና በእግዚአብሔር መንግሥት ርስት የለውም።** ከዚህ የተነሣ በማይታዘዙት ልጆች ላይ የእግዚአብሔር ቁጣ ይመጣልና ማንም በከንቱ ንግግር አያታልላችሁ። እንግዲህ ከእነርሱ ጋር ተካፋዮች አትሁኑ፤ ቀድሞ ጨለማ ነበራችሁና፥ አሁን ግን በጌታ ብርሃን ናችሁ፤ የብርሃኑ ፍሬ በበጎነትና በጽድቅ በእውነትም ሁሉ ነውና ለጌታ ደስ የሚያሰኘውን እየመረመራችሁ፥ እንደ ብርሃን ልጆች ተመላለሱ፤ **ፍሬም ከሌለው ከጨለማ ሥራ ጋር አትተባበሩ፥ ይልቁን ግለጡት እንጂ፥ እነርሱ በስውር ስለሚያደርጉት መናገር እንኳ ነውር ነውና፤ ሁሉ ግን በብርሃን ሲገለጥ ይታያል፤ የሚታየው ሁሉ ብርሃን ነውና።**” (ኤፌሶን 5፡3-13)

(እንደማስተዋወቂይ በመሃል በትሬይለር መልክ የሚገባ አንቂ መረጃ!)
በሴትና በወንድ ድምጽ - በኢንፎርሜሽን ሰጪነት (ፕሮፌሽናል ቶን)

## ይሄንን ያውቁ ኖርዋል?

- ኤድስ ለመጀመሪያ ጊዜ የተገኘው 1981 በግብረሰዶማውያን መካከል እንደነበረና ከዚህ ቀደም ስሙ ግሪድ (ማለትም፤GRID - Gay Related Immune Disorder) ይባል እንደ ነበረ[1] ያውቁ ኖሯል? ግብረሰዶማዊነት አራማጆች ባደረጉት ብዙ ቅስቀሳ ስሙ ኤድስ (Acquired Immune Deficiency Syndrome) ሊባል ችሏል።
- በተደጋጋሚ በተለያየ ቦታ በተደረጉ ጥናቶች እንደሚታየው ግብረሰዶማውያን ልጆችን በመድፈር በተፈረደባቸው ግለሰቦች ስታቲስቲክስ ውስጥ በፐርሰንት ከሄትሮሴክሹአሎች ይልቅ ብዙ ጊዜ እጥፍ ልጆችን ደፋሪዎች (ፒዶፋይሎች) ሆነው እንደሚገኙ ያውቁ ነበርን?
- 

## ዋቤ መጽሐፍት


- *A Parent's Guide to Preventing Homosexuality*, Joseph Nicolosi & Linda Ames Nicolosi, 2002, InterVarity Press
- መጽሐፍ ቅዱስ (የ1954ቱ እትም)

ጽሑፎች/Articles:
Selling homosexuality to America, Paul E. Rondeau.

የዶክትሬት የመመረቂያ ጽሑፍ፤


[1] AIDS was first reported June 5, 1981, when the U.S. Centers for Disease Control and Prevention recorded a cluster of *Pneumocystis carinii* pneumonia (now still classified as PCP but known to be caused by *Pneumocystis jirovecii*) in five homosexual men in Los Angeles.[127

*Assessments of HIV/AIDS related risks among Men having sex with Men (MSM)*, Seifu Hagos, Addis Abeba University, School of Graduate Studies, Department of Community Health, Faculty of Medicine

**የተጠቀምንባቸው ድረ ገጾች፤**

- http://www.metacafe.com/watch/1294305/drug_addiction_crime_homelessness/
- http://crackle.com/c/Movies_and_TV/1969_Scare_Video_Teen_Teenage_Illegal_Drug_Abus_/2349946
- http://video.google.com/videoplay?docid=8251974378917740291&ei=FDogScXGM4-G2QKWtdD2Bg&q=drug+addiction&hl=en
- http://www.dailymotion.com/video/x6b8tp_heroin-facts-the-effects-of-smoking_shortfilms
- http://www.youtube.com/watch?v=4dZl2q13v34
- http://www.broadcaster.com/clip/20654
- http://www.youtube.com/watch?v=BpQONgeB08o
- http://www.narth.com/
- http://christiananswers.net/q-eden/edn-f019.html
- http://gluefox.com/kontr/homo.shtm
- http://www.religioustolerance.org/hom_unchr.htm
- http://www.leaderu.com/jhs/reisman.html
- Google videos
- http://www.lifeissues.net/writers/rond/shta/shta_01sellinghomosexuality1.html
- http://www.google.se/
- http://sv.wikipedia.org/
- http://www.iyesus.com/

**ሌሎች መረጃዎች፤**

**በዶክተር ሮን ሊንዴን በስዊድንኛ የተዘጋጀ ዘጋቢ ፊልም፤** <<Avslöjande Myter Om Sexuell Orientering augusti 2006>> (**ወሲባዊ ዝንባሌን በተመለከተ አሳሳች የሆኑ መላምቶችን ማጋለጥ - ኦገስት** 2006)

**ከዚህ ቀደም** በኢየሩሳሌም ወንጌላዊት ቤተክርስቲያንና በዩናይትድ ፎር ላይፍ ኢትዮጵያ ተዘጋጅተው **(በአዘጋጆቹ) የቀረቡ ዘጋቢ ፊልሞች፤**

1. በኢየሩሳሌም ወንጌላዊት ቤተክርስቲያን <<የምእራባውያን አገሮች ሃይማኖት - ሂውማኒዝም>> የሚልና
2. በዩናይትድ ፎር ላይፍ ኢትዮጵያም <<የድምጽ አልባዎች ድምጽ>>

የሚሉት ይገኙባቸዋል።

**ወደፊት ዘጋቢ ፊልሞች ሊዘጋጅላቸው ከሚታሰቡ ርእሶች መካከል፤**

3. ፌሚኒዝም
4. የፀረ-ሴም መንፈስ (አንቲ-ሴሜቲዝም)